# የሶሻሊስት ሀገሮች ዜጎች
# መሠረታዊ መብቶች ነፃነቶችና ግዴታዎች

ለሕዲሪኢ ምሥረታ
የሰው ኃይል ሥልጠና የተዘጋጀ

ታህሣሥ 1978
አዲስ አበባ

# የሶሻሊስት ሀገሮች ዜጐች
# መሠረታዊ መብቶች ነፃነቶችና ግዴታዎች

ለሕዲሪኢ ምሥረታ
የሰው ኃይል ሥልጠና የተዘጋጀ

ታህሣሥ 1978
አዲስ አበባ

# ማውጫ


| አርዕስት | ገጽ |
|---|---|
| መግቢያ ............................. | 1 |
| **ክፍል አንድ** | |
| ዜግነት፣ መብት፣ ነፃነትና ግዴታ .................. | 7 |
| 1. ዜግነት ........................... | 7 |
| 2. መብት ............................ | 13 |
| 3. ነፃነት ........................... | 18 |
| 4. ግዴታ ............................ | 19 |
| **ክፍል ሁለት** | |
| የዜጎች መሠረታዊ መብቶች፣ ነፃነቶችና ግዴታዎች ........ | 22 |
| 1. የእኩልነት መብት ..................... | 23 |
| 2. የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊና የባህል መብቶች ...... | 27 |
| 3. የሲቪልና የፖለቲካ መብቶችና ነፃነቶች ....... | 39 |
| 4. የዜጎች መሠረታዊ ግዴታዎች .............. | 47 |
| መደምደሚያ .......................... | 50 |
| የግርጌ ማስታወሻ ....................... | 54 |
| ዋቢ መጻሕፍት ......................... | 57 |

## መግቢያ

ለእውነተኛ የሰው ልጅ እኩልነት፣ መብትና ነፃነት በግንባር ቀደም የታገሉ ተራማጅና ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች የከፈሉት መራራ መስዋዕትነትና በየፈርጁ የተቀዳጁት አሸብራቂ ድል ዛሬ አለምን በሁለት ታላላቅ ተፃራሪ ጎራዎች እንድትከፈል አድርጓታል።

ባንድ በኩል ከታላቁ የጥቅምት ሶሻሊስት አብዮት ፍንዳታ በኋላ የተጸዐና አድማስ ከለሉ በየጊዜው እየተጣበበበት በመምጣቱ አብዮት በፈነዳባቸው አገሮች ላይ ሁሉ አድኃሪ የጦረኝነት ተንኳሽ ጣቃን እየሰነረ በመወራወት ሲያፈገፍግ የሚታይ የኢምፔሪያሊስቶች ጎራ ነው። ይህ ጎራ ለግል ንብረት ሥርዓት መስፈንና ጥቂቶች የኅብረተሰብ ክፍል ላቀፈው የገዥ መደብ ጥቅሞች መጠበቅ የቆመ ነው። የሰው በሰው መበዝበዝና መጨቆን የኅልውናው መሠረት በመሆኑ ወደፊት በዚህ ጽሑፍ አንደሚታየው የራሱን ዜጎች እኩልነት፣ መብትና ነፃነት በአፍአዊ ደረጃ እንኳን የሚያውቀውና የሚቀበለው በከፊል ብቻ ነው። በዚህ ማኅበራዊ፣ ኤኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ፍትሕ በሌለበት ሥርዓት ውስጥ እየተጣበበበት በመጣው ይዞታውም እንኳን ሊወጣው በማይችለው ውስብስብ የውስጥ ቅራኔዎችና ማኅበራዊ ችግሮች መወጠሩ የውድቀቱን መቃረብ የሚያመለክት አንድ ምልክት ሆኗል።

ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ በአንዳንድ አገሮች ውስጥ በተካሄዱት ሶሻሊስትና ዲሞክራሲያዊ አብዮቶች የተነሳ ሶሻሊዝም ከአንድ አገር ዳር ድንበር አልፎ የዓለም አቀፍ ሥርዓት በመሆኑ ምክንያት ሌላው ታዳጊና ጠንካራ ጎራ ሊፈጠር ችሏል። ይህ ጎራ የምርት መገልገያዎችን የወል ባደረጉ፣ ብዝበዛንና ጭቆናን ባስወገዱና በማስወገድ

ላይ ባሉ፣ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ወይም በላቀ የዕድገት ደረጃ ላይ የሚገኙ መንግሥት በመሠረቱ ኢኮኖሚያቸውን በማዕከላዊ ፕላን በሚመራ ሶሻሊስት አገሮች የተገነባ ነው። አብዛኛዎቹ ኢትዮጵያን ጨምሮ የሶሻሊስት ዕድገት ፈለግ ተከታይ አገሮች በተራማጂያዊ ገብና ጎዳና ከሶሻሊስት አገሮች ጋር አንድነት ያለው በመሆኑ በዚሁ ጎራ ስር ሆነው ስለዓለም ሠርቶአደር ሕዝብ እኩልነት፣ መብትና ነፃነት፣ እንዲሁም ለሶሻሊዝምና ለዲሞክራሲ በመታገል ላይ ናቸው። ተከከሰቸውን የዕድገት ፈለግ በመምረጣቸውም ከጎራቸው የሚደገፍ የሌሎች አገሮች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ነው። ከራሱ ካፒታሊስት ጎራ ውስጥም የነ ሠርቶአደሮችና ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ለሶሻሊዝም፣ ለእውነተኛ እኩልነትና ለሰው ልጆች መብትና ነፃነት የሚያደርጉት ትግል እያደገ በመምጣቱ የገዢ መደቦችን በማሸበር ላይ ይገኛሉ።

በሠራተኛውና በኮሙኒስት ፓርቲዎች የተቀናጀና የታቀደ ትክክለኛ አመራር ሶሻሊዝምን በመገንባት ረገድ ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል። ከፍተኛ ውጤትም ታይቷል። በዚህም መሠረት ዛሬ ትላልቆቹ የሕዝቡ እኩልነት፣ መብትና ነፃነት በላቀ ደረጃ እንዲረጋገጥና ቁጥጥርም እንዲያገኝ የሚያስችል ዕድገት በየመስኩ በማስመዝገብ የዳበረ ሶሻሊስት ኅብረተሰብ በመገንባት ላይ ያሉ አገሮችን እንደ ገደቡ ለማድረግም በመጋበዝ ላይ ናቸው።

ከዚህ በላይ በተዘረዘሩት ሁኔታዎች ጎራ ሥር የሚገኙት ሶሻሊስት አገሮች በነፃነት አዲስ የፖለቲካ ሥርዓት እየታገዙ በየጊዜው ያዳበሩትን ሶሻሊስት የምርት ግንኙነት ጋብቻውና በየአቅ በመዘርጋት ለእውነተኛ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፍትሕ መሠረትን አነቃቃሽ መሠረት ጥለዋል። ይህም የዜጎችን መብትና ነፃነቶች ለማረጋገጥ የሚያስችሉ

ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ መሠረት ከመሆኑም በላይ የላዕላይ መዋቅሩም የተሟላ ድጋፍ በመታከሉ መብቶቹን በተግባር ለመተርጐም የሚያጋጥም ችግር የለም::

መብቶች ከግዴታዎች ጋር በጥብቅ የተቆራኙ እንደመሆናቸው ለመብቶች በሚገባ መከበር የዜጎች ግዴታቸውን መወጣት የግድ አስፈላጊ ነው:: በመሆኑም ስለ መብት በሚነሳበት ጊዜ ስለግዴታ ሳይወሳ ቢታለፍ ጉድለት ያለው ግንዛቤ መጨበጥ ስለሚሆን ሁለቱንም በእኩል ደረጃ ማጥናት ተገቢነት ይኖረዋል:: ርዕሱ በተኮከለ እንደሚያመለክተው ይህ ክፍል ከሞላ ጎደል በዚሁ አበይ ጉዳይ – በሶሻሊስት አገሮች ዜጎች መሠረታዊ መብቶችና ግዴታዎች – ላይ የሚያተኩር ይሆናል::

የአጠሬያ ዋና ዓላማ የአንድን ሥርዓት የዜጎች መብቶችና ግዴታ ዎች ማስተዋወቅ ነው:: ይህም በኅብረተሰብ የዕድገት ደረጃ ከፍተኛውን ቦታ ይዞው በመምራት ላይ በሚገኙት ሶሻሊስት አገሮች ውስጥ በመንግ ሥትና በዜጎች መካከል የተጣጣመና የሰመረ ግንኙነት መመሥረቱን፣ ለም ርት ኃይሎች ዕድገትና ለሠርቶ አደሩ ሕዝብ ዘላቂ ግብ መሳካት አመቺ ሁኔታ መፈጠሩን ለመገንዘብ እንደሚረዳ ይታመናል::

በዚሁ ጽሑፍ ውስጥ መጀመሪያ የጽሑፉን ርዕስ ስለሚያጎላቸው ጽን ሰ ሃሳቦች ማለትም ስለዜጎች /ዜግነት/፣ መብት፣ ነፃነትና ግዴታ ምን ነትና ታሪካዊ ዕድገት በቀደም ተከተል በየተሰጣቸው ቦታ ይገለጻሉ:: ከዚያም በመቀጠል የሶሻሊስት አገሮች ዜጎች መሠረታዊ ሕግ መንግሥታዊ መብቶችና ግዴታዎች በጥቂቱ እየተዘረዘሩ ይተነተናሉ:: እንዴት በተግ ባር እንደሚተረጎሙ የአንዳንድ አገሮችን ልምድ በምሳሌነት በመውሰድ ለማብራራት ይሞከራል:: ለማነጻጸር ያህል ከሌላው ጎራ የአንዳንድ

ካፒታሊስት አገሮች ዜጎችን መብቶች የሚመለከቱ ሁኔታዎች አልፎ አልፎ ይጠቀሳሉ:: ብዙ ማለት ሲቻል አንዳንድ ሁኔታዎችን ብቻ አልፎ አልፎ መጥቀስ የተመረጠውም ይህ ጽሑፍ እንዲጠና ቀቀ የተፈቀደለት ቦታ ውሱን በመሆኑ እንጂ ገለጻ በሚደረገባቸው የመብቱና ነፃነት ዓይነቶች ላይ ሁሉ መነሳት የሚገባቸው ብዙ ሁኔታዎች ሳይነሱ መቅረታቸውን አዘጋጁ በቅድሚያ ማስገንዘብ ይወዳል::

በዚሁ አጋጣሚ ገለጽ መሆን ያለበት አንድ ነጥብ አለ:: ይኸውም በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የተገለጹት መብቶች በሶሻሊስት አገሮች ሕገጋተ መንግሥት የታወቁና ዋናዎቹ እንጂ በሌሎች ሕጎች የሚታወቁ እያሉ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ፣ ባሕላዊ፣ ፍትሐዊ ወዘተ . . . መብቶችና ነፃነቶች መኖራቸው ሊታወቅ ይገባል:: ከዚህም በቀር የወደፊቱ የኅብረተሰብ ዕድገት ደረጃ የሚወስደው የሕዝብ ፍላጎት የመብትና ነፃነት ጥያቄ ሊሆን ይችላል::

" የሶሻሊስት አገሮች ዜጎች መብቶች፣ የነፃነቶችና ግዴታዎች" በማለት በጥቅሉ ሲገለጽ አንድ ሊነሳ የሚችል ጥያቄ ሊኖር እንደሚችል ማሰብ ይቻላል:: ይህም የብዙዎችን ሶሻሊስት አገሮች ዜጎች መብቶች፣ ነፃነቶችና ግዴታዎች ከሌላው ሶሻሊስት አገር የተለዩ አይደሉም:: በአጠቃላይ የአንዱ ከሁሉም፣ የሁሉም ከአንዱ የተለየ ባለመሆኑ ነው ስለሶሻሊስት አገሮች ዜጎች መብቶች፣ ነፃነቶችና ግዴታዎች በጥቅሉ መናገር የሚቻለው:: ይህም ማለት ግን ምንም ዓይነት ልዩነት ሳይኖር በሶሻሊስት አገሮች ሁሉ የዜጎች መብቶች፣ ነፃነቶችና ግዴታዎች በተመሳሳይ ሁኔታ ሕጋዊና ቁሳዊ ዋስትና ያገኛሉ ማለት አይደለም:: የየሀገሮቹ የዕድገት ደረጃ በመብቶችና ነፃነቶች ተገባራዊነት ላይ መጠነኛ ልዩነትን ሊፈጥር እንደሚችል መገንዘብ ያሻል::

ሕዝባዊት ዲሞክራሲያዊት ሪፑብሊክ ኢትዮጵያን ዜጎች መሠረታዊ መብቶች፣ ነፃነቶችና ግዴታዎች ማጥናት ማለት መሆኑ ግልጽ ነው::

ከዚህም በማነሳት ቀጥሎ ስለዜግነት፣ ስለመብት፣ ስለነፃነትና ስለግዴታ ጽንሰ ሃሳቦች ምንነትና ታሪካዊ ዕድገት በቅድሚያ አጠቃላይ ትንተና ይደረጋል::

# ክፍል አንድ

## ዜግነት፣ መብት፣ ነፃነትና ግዴታ

ስለዜጎች መብት፣ ነፃነትና ግዴታ በሚቀርብ ይህን መሰል ጽሑፍ ላይ በቀጥታ የመብት፣ የነፃነትና የግዴታ ዓይነቶችን ለመግለጽ ከመሞከር ይልቅ በቅድሚያ ርዕሱን ባቋቋሙት ቃላት ጽንሰ ሃሳቦች ምንነት መጀመሩ የበለጠ ግልጽ ለመሆን እንደሚረዳ ስለሚታመን የሚመረጥ ነው:: በዚህም መሠረት ስለዜግነት፣ ስለመብት፣ ስለነፃነትና ስለ ግዴታ ጽንሰ ሃሳቦች ምንነት እንዲሁም ስለፅንሰ ሃሳቦች አመጣጥና ታሪካዊ ዕድገት እንደቅደም ተከተላቸው ከዚህ በመቀጠል ይቀርባሉ::

### 1. ዜግነት

እዚህ ላይ በቅድሚያ ስለዜግነት ምንነት ለማስተዋወቅ የታሰበው የጽሑፉ ርዕስ የዜጎችን መብት፣ ነፃነትና ግዴታ የሚመለከት በመሆኑ በሰዋሰው አነጋገር "ዜጋ"/Citizen / ከሚለው ስም ይልቅ "ዜግነት" /Citizenship / የሚለውን አርዕስት በመውሰድ ስለጽንሰ ሃሳቡ ምንነትና ታሪካዊ እድገት ለመግለጽ መሞከሩ የሚሻል በመሆኑ ነው::

በየትኛውም በመደብ በተከፋፈለ ኅብረተሰብ ውስጥ የሚገኝ ግለሰብ ከመንግሥት ጋር የሚኖረው ግንኙነት በሕግ የተወሰነ ነው:: በዚህ ግንኙነት መሠረት የሚፈጠረው የግለሰቡ ሕጋዊ አቋም የሚወሰነውም በመንግሥት እንደመሆኑ መጠን ግለሰቡ እንደሚገኝበት የኅብረተሰብ ዕድገት ደረጃና መደብ አቋሙ የተለያየ ይሆናል::

በዝባዥ መደቦች ባሉበት ሥርዓት የሚገኝ የማንኛውም ግለሰብ ሕጋዊ አቋም ግለሰቡ ከታቀፈበት መደብ አቋም የተለየ አይሆንም:: ግለሰቡ

መሠረት የወጡ ዜጎች ለሶቭዬት ኅብረት ዜጎች በተሰጡ መብቶችና ነፃነቶች ተጠቃሚዎች ቢሆኑም የመምረጥና የመመረጥ፣ በአገር አቀፍ ውሣኔ ሕዝብ የመሳተፍ መብት የላቸውም:: በሶቭዬት ኅብረት ጦር ኃይሎች ውስጥ የማገልገል ግዴታም የለባቸውም::[2]

ዜግነት ባንዱ በኩል ግለሰብ ለመንግሥት ታማኝና ታዛዥ በመሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ መንግሥት የግለሰቡ ጠባቂና ጥቅም አስከባሪ በመሆን በመንግሥትና በግለሰብ መካከል የጸና ሕጋዊ ግንኙነት ይፈጥራል:: በዚህ ግንኙነት የተቆራኘ ግለሰብ ነው ለመንግሥት ዜጋ ሆኖ በመብቶቹ ተጠቃሚ፣ በግዴታዎቹም ተጠያቂ የሚሆነው:: ይህ የመንግሥትና የዜጋ ሕጋዊ ግንኙነት በሕገመንግሥትና በሌሎች ሕጎች የዜጎችን መብቶች፣ ነፃነቶችና ግዴታዎች እንዲሁም የመንግሥትን ሥልጣንና ኃላፊነት በመከለል የየበኩላቸውን የእንቅስቃሴ ወሰን እንዲለይ ያደርጋል::[3] ለምሳሌ የሶቭዬት ኅብረት የ1978 የዜግነት ሕግ የሶቭዬት ኅብረት ዜጎች የተቀዳጇቸው የሶሻል፣ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካና ግለሰባዊ መብቶችና ነፃነቶች በሕገመንግሥቱና በሌሎች ሕጎች የታወቁና ፀንተና የተሰጧቸው መሆኑን፣ የሶቭዬት ኅብረት መንግሥትም እነዚህን የዜጎቹን መብቶችና ነፃነቶች የሚጠብቅና በኢኮኖሚ፣ በፖለቲካ፣ በማኅበራዊና በባህል መስኮች የዜጎችን እኩልነት የሚያረጋግጥ መሆኑን፣ ዜጎችም ሕገመንግሥቱንና ሌሎች ሕጎችን የማክበር፣ የሶቭዬት ኅብረትን የዜግነት ክብር የመጠበቅ፣ የመንግሥትን ጥቅሞች የመከላከል፣ ለሶሻሊስት እናት አገር እውነተኛና ታማኝ የመሆን ግዴታ[4] ያለባቸው መሆኑን በማረጋገጥ በመንግሥትና በዜጋ መካከል ያለውን ግንኙነት በሕጉ መቅድም አመልክቷል:: በዚህም የዜግነትን ምንነት፣ የሚያስገኘውን ጥቅምና የሚያስከትለውን ኃላፊነት ገልጸ አደርጓል::

ዜግነት ኅብረተሰብ በመደብ ከተከፋፈለበት ከባሪያ አሳዳሪው ሥርዓት ጀምሮ የታየ ክስተት ነው:: የባሪያ አሳዳሪውን ሥርዓት ባስተናገደው በጥንቱ የሮማ ኅብረተሰብ ውስጥ ምንም ዓይነት መብትም ሆነ ንብረት ካልነበራቸው ባሮች ሌላ ዜጎችና ዜጋ ያልሆኑ ነዋሪዎች በመባል የሚታወቁ ግለሰቦች ነበሩ:: ዜጎች የተሟላ መብት ነበራቸው:: ዜጎች ያልሆኑ ግን መብት አልነበራቸውም::[5]

የዲሞክራሲ ጽንሰ ሃሳብ በፈለቀባትና በዳበረባት በጥንታዊቷ የግሪክ ሪፐብሊክ ባሮች እንደዜጎች መቆጠራቸው ቀርቶ እንደሰብዓዊ ፍጡሮች እንኳን አይታዩም ነበር:: "የሚናገሩ ዕቃዎች" ተደርገው ያለምሕረት ይበዘበዙና ይጨቆኑ ነበር:: የዜጎች /ነፃ ሰዎች/ መብቶች ግን በሕግ የተጠበቁና ብዛትም የነበራቸው ናቸው:: በሮማና በአቴና በባሮችና በዜጎች መካከል የነበረው የደረጃ ልዩነት በጣም ሰፊ ነበር::[6]

አብዛኛው የፊውዳሉ ሥርዓት የመጀመሪያ ገጽታ ሲታይ ገባሩ ለመሬት ከበርቴው ከፍተኛውን የሥራውን ውጤት በማስረከብ፣ ልዩ ልዩ ግብር በዓይነት በመክፈልና ነፃ የጉልበት አገልግሎት በመስጠት ፊውዳላዊ ግዴታውን መወጣት ነበርበት:: የመሬት ከበርቴውም ለገባሩ አንዳንድ ጥበቃዎችን ማድረግ ለራሱ ጥቅም መከበር የሚበጀው በመሆኑ ከዚህ የተለየ ብዙም ኃላፊነት አልነበረበትም:: ይህ የመሬት ከበርቴውና የገባሩ ግንኙነት ከባርነት ትንሽ የተሻለ የገባርነት መብትን ያስገኘ ቢሆንም ገባሩ ከሰፈረበት የመሬት ከበርቴው ርስት በፈቃዱ ለቆ የመሄድ ችሎታ እንኳን አልነበረውም:: ይህ ዓይነቱ ግንኙነት በአብዛኛው የቆየው ማዕከላዊው የፊውዳል መንግሥት እስከተጠናከረበት ጊዜ ነበር:: የኋላ ኋላ የዘውዱ አገዛዝ እየተጠናከረ በመምጣቱ በመሬት ከበርቴውና በገባሩ መካከል የነበረው ግንኙነት /ገባርነት/ ኢኮኖሚያዊ መሆን ስለጀመረ

በግለሰብና /ገባር የነበረው/ በማዕከላዊው የፊውዳሉ መንግሥት መካከል ሆነ:: ይህ ዓይነቱ ግንኙነትም የዘውዱ ገባር /ተገዥ/ ያደርገዋል::

በአውሮፓ የፊውዳሊዝም ዕድገት ማኅበራዊ የሥራ ክፍፍልን፣ ይህም በበኩሉ የከተሞች መቋቋምን የንግድና የዕደጥበባት መስፋፋትን በማስከተሉ ወደከተማ እየጐረፉ የሚገቡት ሰዎች ቁጥር እያደገ መጣ:: የከተማ ነዋሪዎችም አንዳንድ የፖለቲካና የንብረት መብት አገኙ:: ዜጎች ተብለው ተቆጠሩ፣ ዜጋ ማለትም የከተማ ነዋሪነትና የአንዳንድ መብቶች ባለቤት መሆን ማለት ሆነ:: አሁንም ቢሆን የዜግነት ባለመብቶች ታላላቅ ነጋዴዎችና የምርት መገልገያ ባለይዞታዎች ብቻ ነበሩ::[7]

ይህ በዚህ እንዳለ በፊውዳሉ ሥርዓት ጉያ ተፈልፍሎ ዕድገቱ በፊውዳሊዝም አድኃሪ መዳፍ ጫና ታፍኖ በመጎሳቆል ላይ የነበረው ታዳጊው ቡርዧ "ገባርነት ያከትማል፤" "ከእንግዲህ ማንም ሰው ገባር አይሆንም፣" "ነፃነት፣ እኩልነት፣ ወንድማማችነት" በሚሉት መፈክሮች ሥር ቶአደረገ ሕዝብ በማሰባሰብ ከጐኑ ማሰለፍ ችሎ ነበር:: እንደሩሶ የመሳሰሉት ታዋቂ የፖለቲካ ፈላስፋዎች ስለዜግነት መተንተን ጀምረው ነበር:: ሩሶ ዜግነት ማለት ግለሰቦችን በመንግሥት ሥልጣን ውስጥ እንዲሳተፉ የሚያደርግ የእኩልነት ስሜት መግለጫ ነው ብሏል:: ከዚህም በመቀጠል በዜግነትና በገባርነት መካከል ስላለው ልዩነት በማብራራት ዜጎች በከፍተኛው የመንግሥት አመራር መካፈል የሚችሉ፣ ገባሮች

---

በዚህ አገባብ(subject) የሚለውን የእንግሊዝኛ ቃል ለመግለጽ ገባር/ተገዥ/ ተብሏል:: ግለሰቡ ከፊውዳል ባላባቶች ጋር የፈጠረውን(serfdom) ግንኙነትንም ለመግለጽ ይህንኑ ቃል ማለትም ገባርነት/ገባር/ በመጠቀማችን ቃሉ ለየትኛው ጽንሰ ሃሳብ እንደዋለ ለመረዳት የቃሉን አገባብ ማጤን ያስፈልጋል::

ግን የመንግሥት ሕጎችን የማከበር ግዴታ ያለባቸው ግለሰቦች መሆናቸ
ውን አመልክቷል:: ለሰዎች አኩልነትም ተከራከሯል::[8]

የሩሶና ተከታዮቹ ሃሳቦች በቡርዧው አብዮቶች ላይ ተጽዕኖ አሳድ
ረዋል:: በፈረንሣይ የ1989 " የሰው ልጅና የዜጋ መብቶች አዋጅ"
መውጣት የመብት መንፈጊያ የጥቆና ምንጭ የሆነውን የገባርነትን መወገድ
እና በምትኩም በፖለቲካ ሕይወት መሳተፍ የሚያስችል የቡርዧውን የዜግ
ነት ጽንሰ ሃሣብ መከሰት አበሰሯል::

ቡርዧው በመሠረተው ማዕከላዊ መንግሥት ሥር የሚተዳደረውን አገር
አንድነት በይበልጥ ለማጠናከርና ለመጠበቅ፣ እንዲሁም የፖለቲካ የበላይ
ነቱን አስተማማኝና ዘላቂ ለማድረግ የዜግነትን መብት ለሁሉም የኅብረ
ተሰቡ አባሎች/ግለሰቦች/ በማዳረስ ከመሬት ከበርቴው የገዥ መደብ የተ
ሻለ መሆኑን ማስመስከር ችሏል::[9] ይሁን እንጂ የቡርዧው ዜግነት ከቀ
ደምቶቹ ጋር ሲነጻጸር የላቀ ቢሆንም ዜግነት የሚያስከትላቸውን መብቶ
ችና ነፃነቶች በእኩልና በተከበለ ለኅብረተሰቡ አባላት ማዳረስ አይሆን
ለትም::

ቀደም ሲል ፋጽም ይታወቅ ያልነበረው የመንግሥትና የዜጋ የሰመረ
ግንኙነት በዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነትና በሶሻሊስት ሕጋዊነት መርሆች
ላይ ተመስርቶ የተገነባው የቡርዧውን ሥርዓት በተካው በሶሻሊዝም ነው::

የምርት መገልገያዎች የግል ይዞታ ተወግዶ በሕዝብ የጋራ ይዞታ
የተተካው፣ የሰው በሰው መበዝበዝ ቦታ ያጣው፣ በመንግሥት ሥራዎች
የሠርቶአደሩ ሕዝብ ሉአላዊነት የተገለጠውና የሶሻሊስት ዲሞክራሲና
ሕጋዊነት የሰፈነው በሶሻሊዝም ነው:: በዚህ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና
ፖለቲካዊ መሠረት ላይ የተገነባው የሶሻሊስት መንግሥትና ዜጋ ግንኙነት

የሰመረና ከቀራኒ የጸዳ ነው:: ይህ ዓይነቱ አዲስ ሶሻሊስት ዜጋም በሶሻሊስት ዲሞክራሲ ምርጫ ሥርዓት የራሱን መንግሥት አቋቁሞ በመምራት፣ ብሔራዊ ሀብቱን በማስተዳደሩና በመቆጣጠር፣ መሠረታዊ ሕጎች አወጣጥ ላይ በውሣኔ ሕዝብ በቀጥታ በመሳተፍ፣ ጥቅሙን የሚጠብቁና ፍላጎቶችን የሚያንፀባርቁ ሶሻሊስት ሕግጋትን ያለአንዳች ማወላወል በማክበርና የማስከበር ሶሻሊስት ሕጋዊነትን በማስፈን የራሱን ዕድል በራሱ መወሰን የቻለ ሰው ነው:: በመደብ ኅብረተሰብ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ከብዝበዛ እና ከጭቆና ነፃ የሆነ ሰው ነው:: በመሆኑም የዜግነት እኩልነት፣ መብትና ነፃነቱ በተሟላ መልኩ ሕጋዊና ቁሳዊ ዋስትና አግኝቶ ለሁለንተና-ሰብዕናው መዳበር በአመቺ ሁኔታ ላይ ያለው ይህ አዲሱ ሶሻሊስት ዜጋ ነው::

ከዚህ በላይ ስለዜግነት ምንነትና ታሪካዊ ዕድገቱ አጠቃላይ የመግቢያ ሃሳብ በመስጠቱ ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ ስለመብት ምንነትና በታሪክ ውስጥ ስላሳየው የዕድገት ሂደት አጭር ገለጻ ይደረጋል::

## 2. መብት

ለዚህ ጽሑፍ አገባብነት ባለው መልኩ መብት ማለት በሕግ የታወቁና በሚመለከታቸው የመንግሥት ተቋሞች አፈጻጸሙ ዋስትና ማግኘት የሚችል የዜጎች /የግለሰቦች/ የይገባኛል ጥያቄ ነው በማለት በጥቅሉ መተርጎም ይቻላል::

መብቶች እንደሚጠብቁት ጥቅም ዓይነት ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ፣ ባህላዊ፣ ፖለቲካዊና /ሲቪል/ ግለሰባዊ ተብለው ይታወቃሉ::[10]

ስለመብት ጽንሰ ሃሳብ አመጣጥና ታሪካዊ ዕድገት በዝርዝር ለማቅረብ መሞከሩ በዚህ ነጥብ ላይ ብቻ ጽሑፉን ማጣበብ ይሆናል። በመሆኑም ጠቅለል ባለመልኩ መመልከቱ ተገቢ ነው።

በባሪያ አሳዳሪው ሥርዓት ባሮች ምንም ዓይነት መብት እንዳልነበራቸውና እንደሰብዓዊ ፍጡርም ይታዩ እንዳልነበረ ቀደም ሲል ተገልጧል። ባሮችን ማራባት /ማቀለድ/ የብዙ ሀብት ባለቤት መሆንን እንደሚያስከትል በመረዳት ሦስት ልጆች የወለደች ባሪያ ከሥራ ነፃ እንድትወጣ፣ ከሦስት ልጆች በላይ የወለደች ከሆነ ደግሞ አርነቷን እንድታገኝ ተደርጓል።[11] ባሪያዋ ብዙ ልጆች ወልዳ ለባሪያ አሳዳሪው ንብረት እንዲሆን በመስጠት ከሥራ የመላቀቅ ወይም ነፃ የመውጣት "መብት" ቢኖራትም፣ ይህ መብት ኢኮኖሚያዊ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ድጋፍ ስለማይሰጠው የይስሙላና ዋጋ የሌለው ሆኖ የሚቀር ነው።

በእንግሊዝ ኅብረተሰብ ታሪክ ውስጥ መካከለኛው ዘመን እየተባለ በሚታወቀው የፊውዳል ሥርዓት በነገሥታቱና በፊውዳሎች መካከል የተደረገው የረጅም ጊዜ ትግል ውጤት የሆነው የ1215 ማግና ካርታ ለከፊሉ የኅብረተሰብ ክፍል ብቻ ቢሆንም ተገቢ መብት አስጠብቋል።

ከ17ኛው ምዕተ ዓመት አጋማሽ በኋላ አንዳንድ የፖለቲካ ፈላስፎች ስለመብት የተለየ ትኩረት በመስጠታቸው የነሱ አስተሳሰብ ለቡርዧው አብዮት መፈንዳት አስተዋጽኦ አድርጓል። በዚህም መሠረት የእንግሊዙ ጆን ሎክ /1632-1704/ የፈረንሣዩ ባሮን ደሞንተስኩ /1639-1755/ እና ዣን ዣክ ሩሶ /1712-1778/ በዚህ ረገድ ሊጠቀሱ የሚገባቸው ፈላስፎች ናቸው። የ1689 የእንግሊዝ፣ የ1789 የፈረንሣዩና የ17-91 የአሜሪካ ሰብዓዊ መብቶች አዋጆች መውጣት በየሀገሮቹ የፈነዱት የቡርዧ አብዮቶች ውጤቶች ናቸው።

እነዚህ አዋጆች የንግግርና የጽሑፍ፣ የመሰብሰብና ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ፣ የመምረጥና የመመረጥ፣ የእኩልነት፣ የነፃነት፣ ወዘተ ... መብቶች እንዲታወቁ አድርገዋል:: ይሁን እንጂ የነዚህ መብቶች ዋናዎቹ ተጠቃሚዎች የምርት መገልገያዎች የግል ባለይዞታዎች የሆኑት የቡርዧው የገዥ መደብ አባሎች ናቸው:: ለሠርቶአደሩ ሕዝብ ግን የይስሙላ መብቶች ሆነው ቀርተዋል:: ሠርቶአደሩ ሕዝብ ከምርት መገልገያዎች ባለቤትነት በመገለሉ በነዚህ መብቶች ለመገልገል የሚያስችሉት ብዙ መሰናክሎች አሉበት:: ለምሳሌ የመሰብሰቢያ አዳራሾች በካፒታሊስቶች የግል ይዞታ ስር እስከሆኑ ድረስ የካፒታሊስቶችን መደብ ጥቅም ሊጎዳ የሚችል ውይይት ለማካሄድና ውሳኔ ለማሳለፊያ አዳራሾችን በምንም ዓይነት ፈቃደኛ ለተጻራሪው መደብ አባላት አይከፍትም::

ሌላ ምሣሌም መጥቀስ ይቻላል:: በካፒታሊስት ሥርዓት የመምረጥና የመመረጥ መብት በሕግ የታወቀ ነው:: ቡርዧው በዚህ መብት ሲጠቀም፣ ለሠራተኛው ግን ተሟልቶ የቀረበለት መብት አይደለም:: የገዥው መደብ በነደፈው የምርጫ ሥርአት መሠረት የሠራተኛው መብት ከካፒታሊስቱ የመደብ ከቀረቡለት ዕጩዎች መካከል አንዱን መምረጥ ብቻ ነው:: የተወሳሰቡ የሕግ፣ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ መሰናክሎች ከፊቱ ተደቀነው ስለሚጠብቁት ሠራተኛው መመረጥ አይችልም:: ይህም ይበልጥ ግልጽ ለማድረግ የአሜሪካን የምርጫ አፈጻጸም መመልከቱ በቂ ነው:: በ1979 ለምክር ቤት /ኮንግረስ/ በተደረገ የምርጫ ውድድር ከሁለት ሚሊዮን እስከ ሦስት ሚሊዮን ብር በላይ ተወዳዳሪዎች ለቀደመ ምርጫ ውድድር ማውጣት ነበረባቸው:: ለአሜሪካ ምክር ቤት አባልነት ለመወዳደር ወሳኙ ሀብት በመሆኑ ማንኛውም ሠርቶአደር ሊወዳደርም ሆነ ሊመረጥ ከቶ አይቻለውም:: አሜሪካኖች ራሳቸው ምክር ቤቱን "የሀብታሞች

ጊዜ አብዛኛው የኅብረተሰብ ክፍል ብሎም ሁሉም የኅብረተሰብ አባል በመብቶቹ የሚገለገለው በሶሻሊዝም ነው።

የቡርዧው አብዮት ሲቃኘው ሌሎች ኃይሎችን ከጉኑ ያሰባሰበለት አብዮታዊው ቡርዧ መፈክር ከፊውዳል መሳፍንት ጭቆናና ብዝበዛ ነፃ የመውጣት መብት እንዲከበር የሚጠይቅ ነበር። ይሁን እንጂ የቡርዧው አብዮት ግቡን እንደመታ ቡርዧው አብረውት ተሰልፈው የነበረውን የጭቁን መደቦች ጥያቄ ችላ ብሎ ለራሱ መደባዊ ልዕልና መጠናከር ብቻ አጥብቆ በመሥራቱ በመብት ላይ የነበራቸው የጋራ ጥያቄመለያየትን አስከተለ።

ቡርዧው የራሱን የመደብ ጥቅሞች ለማስከበር የምርት መገልገያዎች የግል ይዞታ መብት ሊደፈረ አይችሉም ሲል፣ ወዛደሩ ደግሞ የብዝበዛ ምንጭ የሆነው የግል ንብረት ተቋም ብቻ ሳይሆን መደቦች ራሳቸው መጥፋት አለባቸው ባይ ነው።[13]

ለቡርዧው በምርት መገልገያዎች የግል ይዞታ መሆን ሰውን መበዝበዝና መጨቆን የሰብዓዊ መብት መከበር፣ የምርት መገልገያዎች ይዞታ መሆን የሰብአዊ መብቶችና ነፃነቶች መደፈር ማለት ነው። የተደፈረውም የመበዝበዝ "መብት" ነው እንጂ ሌላ ነገር አይደለም። ይህ በመዛደሩ ዘንድ የሚታየው በተቃራኒው ነው። የምርት መገልገያዎች ይዞታ ማኅበራዊ መሆን ማለት የወዛደሩ ከብዝበዛ ነፃ መውጣት ማለት ነው። ወዛደሩ የሚታገለውም ያለመበዝበዝ መብቱን ለማስከበር ነው። ይህ የወዛደሩ ትግል አሸናፊ በመሆን የምርት መገልገያዎች ይዞታ ማኅበራዊ በሆነባቸው በሶሻሊስት አገሮች እውነተኛ የዜጎች የሶሻል፣ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካና ግለሰብአዊ መብቶችና ነፃነቶች መከበር ችለዋል።

## 3. ነፃነት

በመሠረቱ በመደብ ኅብረተሰብ ስለነፃነት ተመሳሳይ ግንዛቤ ሊኖር አይችልም—የአንዱ መደብ ነፃነት የሌላው ተፃራሪ መደብ ባርነት ነውና::: በዚህም መሠረት በተለያዩ ሥርዓተ ማኅበሮች የተደረጉ የመደብ ትግሎች ሁሉ የነፃነት ትግል ባህርይ የነበራቸው ናቸው:: በአንድ ታሪካዊ ወቅት የተገኘ ወይም የታጣ ነፃነት ስገል በአንድ የተወሰነ መደብ የተገኘ ወይም የታጣ ነፃነት ማለታችን ነው:: የአንድ መደብ ነፃነት ማግኘት ወይም ማጣት ከሌላ ተቃራኒው መደብ ነፃነት ማግኘት ወይም ማጣት ፍፁም የተለየ ነው:: ስለሆነም ስለነፃነት ምንነት የተለያዩ መደቦች የተለያዩ አመለካከትና ግንዛቤ አላቸው::[14]

በኅብረተሰብ የዕድገት ታሪክ ውስጥ የባሪያ አሳዳሪውን ሥርዓት ብንወስድ የባሪያ አሳዳሪው መደብ ነፃነት ባሪያውን ያላንዳች ገደብ መበዝበዝና መጨቆን ሲሆን፣ የባሪያው መደብ ነፃነት ደግሞ ከባሪያ አሳዳሪው አሰቃቂ ብዝበዛና ጭቆና መላቀቅ ማለት ነበር:: የፊውዳሉና የገባሩ መደቦች የነፃነት ግንዛቤም እንዲሁ ከመደባዊ ጥቅም ውጭ አልነበረም:: ለቡርዧው መደብ ነፃነት ማለት መጀመሪያ ከፊውዳሉ የገዥ መደብ ጋር በነበረው የሞት ሽረት ትግል በአሸናፊነት መውጣት፣ ቀጥሎም አኗኗሩን የካፒታሊስት ስል ተምርት በመመሥረትና በማጠናከር ወዛደሩ የሥራ ሀይል የተፈጠረውን ተረፈ እሴት በማጋበስ የመበዝበዝ መብት ማለት ነው:: ለወዛደሩ መደብ ነፃነት ማለት የካፒታሊስቶን የብዝበዛና የጭቆና ቀንበር ሰባብሮ በመጣል ለወዛደሩ ጭቆና የሌለበት ሥርዓት መመሥረት ነው:: ይህም በወዛደሩ የተቀናጀ ትግል የምርት መገልገያዎችን ይዞታ ወደማኅበራዊነት በለወጠውና የወዛደሩን የበላይ ገዥነት መገን

ሥት በመሠረተው በሶሻሊስት አብዮት ዕውን ሊሆን በመቻሉ ዛሬ የሶሻሊስት አገሮች ዜጎች የእውነተኛ ነፃነት ባለቤቶች ሊሆኑ በቅተዋል::

እውነተኛ ነፃነት ሲባል ጥቂቶች አብዛኛውን የኅብረተሰብ ክፍል የመበዝበዝ ፈቃድ የሚሰጥና ከኅብረተሰቡ ቁጥጥር ውጭ እንዲሆኑ የሚያደርግ ማለት አይደለም:: እውነተኛ ነፃነት ከማንኛውም ዓይነት ኢኮኖሚያዊ በዝበዛ ነፃ መሆንን፣ በሁሉም የጋራ ጥረት ለሚገኝ የተሻለ አስደሳች ሕይወት በአኩል ደረጃ በኅብረተሰቡ የፖለቲካ ሕይወት የመሳተፍ ነፃነትን፣ እንዲሁም የመሥራት፣ የመዝናናት፣ የትምህርት፣ የጤናና ሌሎች ፍላጐቶችን የማግኘት ነፃነትን ያካትታል::[15]

የነፃነት ጽንሰ ሃሳብ አድማስ ሰፊ ነው:: ከዘረኝነት፣ ከቅኝ ግዛት፣ ከብሔር/ብሔረሰብ/ ወዘተ ... ጭቆናና በዝበዛ መላቀቅን እንዲሁም ከተፈጥሮ ቁጥጥር ነፃ መሆንን እንደሚያጠቃልል በአጋጣሚው መግለጹ ተገቢ ይሆናል::

## 4. ግዴታ

በዚህ ጽሑፍ ርዕስ ላይ በተመለከተው አገባቡ ግዴታ ማለት ማንኛውም ዜጋ ከመንግሥት ጋር በፈጠረው ሕጋዊ ግንኙነት መንግሥት ለዜጋው የሕግ ዋስትና ሰጥቶ ለማስከበር ቃል በገባው መብት አንፃር በዜጋ በኩል መደረጋቸው በሕገ መንግሥትና በሌሎች ሕጎች የተወሰኑትን አስገዳጅ ተግባሮችን ለማከናወን ራሱን ተገዥ ያደረገበት ሁኔታ ነው ሊባል ይችላል::

ለመንግሥት፣ ለኅብረተሰብና ለዜጎች ጥቅም ሲባል በዜጋ ላይ ሕግ የጣለው ማናቸውም ግዴታ የግድ መፈጸም ይኖርበታል:: ማንኛውም ዜጋ

በሕግ የታወቀለትን መብቱን ለማስከበር መክሰስ እንደሚችለው ሁሉ ግዴታውን ያልተወጣ ዜጋም በሕጉ መሠረት ተከሶ ሊቀጣ፣ ግዴታውንም እንዲፈጽም ሊገደድ ይችላል::

መብትና ግዴታ ተነጣጥለው ለየብቻቸው እንደሚቆሙ ተደርጎ የሚቀርብበት ጊዜ አለ::[16] ይህ በመሠረቱ ትክክል አይደለም:: መብትን ከግዴታ፣ ግዴታን ከመብት ነጥሎ ለማቆም የሚደረገው ሙከራ የሁለቱን የተጋባሪ ዲያሌክቲካዊ ግንኙነት በማፍረስ ለበዝባዦች መብትን፣ ለሠርቶ አደሩ ደግሞ ግዴታን በማደላደል የበዘበዛና ጭቆና ሥርዓታቸውን ለማራዘም ካላቸው ፍላጎት የመነጨ ነው:: በመሆኑም የ1977 የሶቭዬት ሶሻሊስት ሪፐብሊኮች ኅብረት ሕገመንግሥት አንቀጽ 59 "ዜጋዎች የሚጠቀሙባቸው መብቶችና ነፃነቶች መፈጸም ካለባቸው ተግባሮቻቸውና ግዴታዎቻቸው ጋር የማይነጣጠሉ ናቸው" ብሏል::

በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት መብት ከግዴታ፣ ግዴታም ከመብት ተነጥሎ የሚታይ አይደለም::

ሕገ መንግሥትና ሌሎች ሕጎች የማክበር ሕጋዊ ግዴታ ያለበት ማንኛውም ዜጋ ግዴታውን ከጣሰ፣ የጣሰው መብቱን፣ ነፃነቱንና ጥቅሞቹን ጭምር ያረጋገጠለትንና ያስከበረለትን ሕግ ማለት መሆኑ ለማንም ግልጽ ነው:: ለምሣሌ የሥራ ሥነሥርዓትን በማክበር ግዴታውን መወጣት ያልቻለ ዜጋ ሠርቶ የመኖር፣ የማረፍና የመዝናናት ሕገመንግሥታዊ መብቶቹን የሚያረጋግጠውን ሕግ መጣስ ብቻ ሳይሆን መብቶቹን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችለውን ቁሳዊ ምርትን መፍጠር አይችልም::

በመብቶቹ እየተጠቀመ ግዴታዎቹን የማያከብር ዜጋ ግዴታቸውን በሚያከብሩ ሌሎች ዜጎች ጫንቃ የሚኖር መውሰድ እንጂ መስጠት የማያውቅ

የኅብረተሰብ ጠንቅ ነው፡፡

ከዚህ በላይ በምሣሌ የተጠቀሰውን መብት ተግባራዊ ለማድረግ ግዴታን መወጣት፣ ግዴታን ለመወጣት ደግሞ መብትን ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ ለዚህም ነው ማርክሲስቶች ለመብቶች ብቻ ሳይሆን ለመብቶችና ግዴታዎች እኩልነት በመቆም የመብትና ግዴታን ሚዛን በመጠበቅ በሶሻሊስት መንግሥትና በዜጋ መካከል ያለው ግንኙነት የራቀ እንዲሆን የሚያደርጉት፡፡

## ክፍል ሁለት

## መሠረታዊ መብቶች፣ ነፃነቶችና ግዴታዎች

በዚህ ጽሑፍ መግቢያ ላይ እንደተመለከተው በሁለት ታላላቅ ተፃ
ራሪ ጐራዎች የከተፈለችው ዓለማችን በዜጐች መብቶች ጥያቄ ላይ የር
ዕዮተዓለም ትግል የሚካሄድባት መድረክ ሆናለች:: ከሁለተኛው የዓለም
ጦርነት በኋላ ሰብዓዊ መብቶችንና ነፃነቶችን የሚመለከቱ ከ40 ያላነሱ
ዓለምአቀፋዊና አህጉራዊ ሕጎችና ስምምነቶች የወጡ ቢሆንም [17] በተለይ
ለሠርቶአደሩ ሕዝብ ከፍተኛ ፋይዳ ያላቸው የኢኮኖሚ፣ የሶሻልና የባህል
መብቶች በካፒታሊስት አገሮች ተቀባይነት አላገኙም:: ይህም የወዛደሩ
ጥቅም አራማጅ መሪ የነበረው ካርል ማርክስ "መብት ከኅብረተሰቡ የኢ
ኮኖሚ መዋቅርና የባህል ዕድገት ደረጃ በምንም ዓይነት ሊበልጥ አይችልም" [18] እንዳለው የካፒታሊዝም የኢኮኖሚ አደረጃጀት ዜጐችን /ሠርቶ
አደሮችን/ የነዚህ መብቶች ባለቤቶች ሊያደርጋቸው ፈጽሞ አይቻለውም::
በሶሻሊስት አገሮች ግን እነዚህ መብቶችና ነፃነቶች ሕጋዊና ቁሳዊ
ዋስትና በማግኘታቸው ዜጐቻቸው እየተገለገሉባቸው ነው:: ይሄን እንጂ
ማገኛውም መብትንም ሆነ ነፃነትን የሠርቶአደሩን ሕዝብ ጥቅሞች፣ የ
ሶሻሊዝምንና ዲሞክራሲን በሚጎዳ ሁኔታ መገልገል እንደማይቻል መታወቅ
አለበት::

ቀደም ሲል በዚህ ጽሑፍ ክፍል አንድ ስለዜግነት፣ ስለመብት፣ ስለ
ነፃነትና ስለግዴታ ምንነት፣ ግንኙነትና ታሪካዊ ዕድገት በጥቅሉ መግ
ለጹ የሚታወስ ነው:: ከዚህ በመቀጠል ደግሞ ስለሶሻሊስት አገሮች
ዜጐች መሠረታዊ መብቶች፣ ነፃነቶችና ግዴታዎች አይነቶች ጠቅለል ባለ
መልካቸው ይዳሰሳሉ:: ለዚህ ጽሑፍ አቀራረብ ያመች ዘንድ ከሚከተለው

ዓይነትና ደም ተከ ተሰ መሠረታዊ ሕገመንግሥታዊ መብቶችን፣ ነፃነቶችንና ገጽታዎችን እንመለከታለን::

1. የዐኩልነት መብት
2. የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊና የባህል መብቶች
3. የሲቪልና የፖለቲካ መብቶችና ነፃነቶች
4. ገጽታዎች

## 1. የዜጎች እኩልነት መብት

በዚህ ክፍል ውስጥ የእኩልነት መብት ከሌሎች መብቶች ሁሉ ቀደም ቦታ የተሰጠው ወደፊት አገባብ ባለው ስፍራ በዝርዝር በምናያቸው ሌሎች የዜጎች መብቶችና ነፃነቶች በመገልገል ረገድ በዜጎች መካከል ልዩነት ሳይደረግ በእኩል ደረጃ የሚታዩ መሆናቸውን በቀዳሚያ ማሳየቱ ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ ነው::

በመሠረቱ "በሕግ ፊት እኩልነት" በቡርዧው ፈጠራ ነው:: ከፊውዳሊዝም ጋር በነበረበት ትግል በመፈክርነት የተጠቀመበትና ሌሎች አገሮችን የሳበ ተራማጅ አስተሳሰብ ነበር::ቡርዧው ከትግሉ በአሸናፊነት ቢወጣም የሕግ ቀነትና ከመስጠት ባሻገር እኩልነትን ተግባራዊ ማድረግ አልቻለም:: በፊውዳሉ ሥርዓት ለሰዎች እኩል አለመሆን ምክንያት የነበረውን የምርት መገልገያዎችን የግል ይዞታ መብት በማጥፋት ፋንታ ራሱም ስለገፋበት እውነተኛ እኩልነትን ማስፈን የሌላ ድርሻና ተልዕኮ መሆኑ ገለጸ ሆነ::

ታዋቂው ሞሪስ ኮርንፎርዝ በትክክል እንደገለጸው እኩልነት ሊረጋገጥ የሚችለው እኩል አለመሆን ሲወገድ ነው:: እኩል አለመሆን የሚወገደውም

የእኩል አለመሆን ምንጮች ሲደርቁ ነው፡፡ የእኩል አለመሆን ምንጮች ደግሞ የምርት መገልገያዎች ይዞታ የግል መሆን፣ የኅብረተሰብ በመደብ መከፋፈልና የሰው በሰው መበዝበዝ ሥርዓቶች ናቸው፡፡[19] እነዚህ የእኩል አለመሆን ምንጮች እስካልጠፉ ድረስ የዜጎችን የእኩልነት መብት በሕግ መደንገጉ ብቻ ፋይዳ አይኖረውም ተግባራዊ የሚሆኑበት ቁሳዊ መሠረት የላቸውምና፡፡

እዚህ ላይ አንድ ምሳሌ መጥቀስ ይቻላል፡፡ በአሜሪካ መንግሥት መግለጫ መሠረት ከጠቅላላው ሕዝብ መካከል 1% የሚሆኑት ቱጃሮች ከሀገሪቱ ጠቅላላ ሀብት ውስጥ 36%፣ እንዲሁም ከጠቅላላው አክሲዮን ውስጥ 61% የሚሆነውን ሲወስዱ፣ 26 ሚሊዮን ዜጎች ግን ከድኅነት ከለል በታች ወርደው ይገኛሉ፡፡ ከእንግሊዝ ብሔራዊ ሀብት ውስጥ ግማሹ የተያዘው 5 % ብቻ በሚሆኑት ዜጎቿ ነው፡፡ 10% የሚሆኑት የፈረንሣይ ዜጎች ከሀገሪቱ ብሔራዊ ሀብት ግማሹን ጨምረው ይዘዋል፡፡[20] እንግዲህ የቡርዧው እኩልነት ይህ ነው፡-ከጠቅላላው ብሔራዊ ሀብት ውስጥ ግማሹን 5% ወይም 10 % የሚሆነው ሕዝብ ብቻ ሲቆራመት፣ ትራፊው ደግሞ 95% ወይም 90% ለሚሆነው ለየሀገሮቹ ዜጋ የሚከፋፈልበት፣ ከዚህም ውስጥ ምንም የማያገኝ ሰው የሚኖርበት፡፡ ይህን ሕጋዊ ባደረገ ሕግ ፊት ነው እኩል ያልሆኑ ዜጎች እኩል ናቸው የሚባለው፡፡ ለዚህ ፍትህ የተጓደለበት ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት ምንጩ የምርት መገልገያዎች ይዞታ ግላዊ መሆን ነው፡፡

በዝባዥና ተበዝባዥ መደቦችን በመፍጠር በሰዎች መካከል ልዩነት /እኩል አለመሆን/ እንዲኖር ያደረገውን የምርት መገልገያዎች ግላዊ ይዞታ አስወግደው አዲስ ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት በመገንባት ላይ ያሉ ሶሻሊስት አገሮች ናቸው፡፡ ለእያንዳንዱ ዜጋ እንደ ሥራው ዓይነትና መጠን

የሚከፈልበትን የመሥራት መብት በማረጋገጣቸው በኅብረተሰቡ መካከል ያለው የማኅበራዊ ኑሮ ደረጃ በጣም እንዲቀራረብ ተደርጓል:: የዜጎችን እኩልነት እውን ለማድረግ የሚያስችሉ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ሁኔታዎች ሰፍነዋል:: በየሀገሮቹ ከመሰረተ በመዳበር ላይ ያለው ሶሻሊስት ዲሞክራሲም ዜጎች በፖለቲካው፣ በኢኮኖሚውና በሌሎች መስኮች በእኩልነት በመሳተፍ የራሳቸውን ጉዳይ ራሳቸው እንዲወስኑ ከፍተኛ ድጋፍ ሆኗል::

ይህን ቁሳዊ መሠረት በማደራጀትና በማጠናከር ነው ሶሻሊስት አገሮች በሕግጋተ መንግሥታቸው የዜጎች የእኩልነት መብት በኢኮኖሚ፣ በማኅበራዊ ኑሮ፣ በፖለቲካና በባህል መስኮች ሁሉ የተጠበቀ ነው በማለት የደነገጉት::[21]

በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ውስጥ በምርት መገልገያዎች ይዞታ ማኅበራዊ መሆን በዝባዥና ተበዝባዥ መደቦች በመጥፋታቸው ዋናው የሰዎች እኩል አለመሆን ምንጭ ደርቋል:: በመሆኑም በዜጎች መካከል ልዩነት ሊያስከትል ይችላል ተብሎ የሚገመተው ሌላ ሁኔታ በዘር፣ በብሔረሰብ፣ በጾታ፣ በሃይማኖት፣ ወዘተ ... መነሻ ከሚፈጠር አድሏዊ የወገናዊነት ስሜት የሚመነጭ ነው:: ይህንንም የማይፈለግ እንከን ለመከላከል ሕግጋተ መንግሥቱ በግልጽ ለዜጎች ዋስትና ሰጥቷል::

በሴቶችና በወንዶች መካከል የእኩልነት መብት በሶሻሊስት አገሮች ሕግጋተ መንግሥት ተረጋግጧል::[22] ሴቶች ከወንዶች እኩል ትምህርት በመማር፣ የሙያ ዕውቀት በመቅሰም፣ በመሥራትና በሥራ መጠንና ዓይነት በመከፈል፣ በማኅበራዊ፣ በፖለቲካዊ፣ በባህላዊ ተግባሮች መሳተፍ፣ የአጸደ ሕፃናትና የሙዓለ ሕፃናት አገልግሎቶችን በማስፋፋትና በመሳሰ

ሉት ይህን መብት ተግባራዊ እንዲሆን ተደርጓል፡፡

በሶሻሊስት አገሮች ለሴቶች እኩልነት ይህ ዓይነቱ ቁገዊና ጠጋዊ ቁከትና ቢስጥም በአንዳንዱ ካፒታሊስት አገሮች ችግሩ ገና አልተቃለ ለም፡፡ ለምሳሌ በአሜሪካ ለሴቶች የሚከፈለው ደመወዝ ከወንዶች በ40 % ያነሰ ነው፡፡[23]

በሶሻሊስት አገሮች ለብሔረሰቦችና ለብሔሮች ጥያቄ ማርክሳዊ ሌኒ ናዊ መፍትሔ ሳንዲና ለመጨረሻው በመስጠት በዲሞክራሲያዊና በእኩልነት ላይ በመሠረት የተገነባው የአገር አንድነትና ኅብረት የጠላትን ሁሉ ሴራና ደባ ያለፈ የማይደፈር ኃይል ነው፡፡ በመሆኑም በዓለም አቀፋዊ ወርኅ መሠረት አንድነትንና ኅብረትን የመሠረቱት ብሔሮችና የብሔረሰቦች ዜጎች የእኩልነት መብት በሕገመንግሥት ተረጋገጠላቸዋል፡፡ የሶቭዬት ኅብረት ሕገ መንግሥት አንቀጽ 36 እንደደነገገው ** ማንኛውም ዓይ ነት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ /የሚደረግ/ የዜጎች መብት እገዳ፣ በዘር ወይም በብሔረሰብ ላይ ተመርኩዞ የሚፈጸም አድልዎ እን ዲሁም ማንኛውም አይነት የዘረኝነት ወይም የብሔረተኝነት ልዩነት ስብ ከት ማሰራጨት፣ መቃቃርንና መናናቅን ለመፍጠር መሻት በሕግ ያስቀጣል፡፡ **የ1960ው የቼኮስሎቫኪያ ሶሻሊስት ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት አንቀጽ 20 ይህንኑ ያስገነዝባል፡፡

ከዚህ በላይ ለመተንተን የተሞከረው ስለዜጎች የእኩልነት መብት ነው፡፡ ቀደም ሲል እንደተገለጸው መብት ከግዴታ፣ ግዴታም ከመብት የማይነጣጠሉ ስለሆነ ዜጎች የግዴታ እኩልነት መብት እንዳላቸውም መታ ወቅ ይኖርበታል፡፡ ይህም ማለት ግዴታቸውን በመወጣት ረገድ የዜጎች ተጠያቂነትና ተጠሪነት እኩል ነው ማለት ነው፡፡

## 2. የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊና የባህል መብቶች

የዜጎች የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊና የባህል መብቶች ለመጀመሪያ ጊዜ
በሕገመንግሥት ውስጥ ተደንገጉ ተግባራዊ መሆን የቻለው በ1936 በሶ
ቭዬት ኅብረት ነው፡፡ ሌሎች ሶሻሊስት አገሮችም እነዚህን መብቶች በመ
ቀበል በሕገጋት መንግሥታቸው እንዲታወቁ አድርገዋል፡፡ የመሠረቱት
ሶሻሊስታዊ የኢኮኖሚ ሥርዓትም መብቶቹን ተግባራዊ ለማድረግ አስተማማኝ
ዋስትና ሆኗል፡፡

ከዜጎች መሠረታዊ ሕገመንግሥታዊ የኢኮኖሚ፣ የሶሻልና የባህል መብ
ቶች መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡ እነሱም፡-

1. የመሥራት መብት
2. የማረፍና የመዝናናት መብት
3. የጤና እንክብካቤ መብት
4. የኑሮ ዋስትና መብት
5. የመማር መብትና
6. ሌሎች መብቶች ናቸው፡፡

ከዚህ በመቀጠል እነዚህን መብቶች አንዱ በአንዱ እንመለከታለን፡፡

### 2.1 የመሥራት መብት

ፍሬደሪክ ኤንግልስ "ሰውን ሰው ያሰኘው ሥራ ነው" ሲል ያለ ሥራ
የሰው ልጅ ሕልውና ሊኖር የማይችል መሆኑን ማመልከቱ ጭምር ነበር፡፡
ማንም ሰው በሕይወት ለመኖር መሥራት አለበት ማለት ነው፡፡ ሠርቶ ለመ
ኖር ደግሞ ሥራው ራሱ መገኘት አለበት፡፡ በምርት መገልገያዎች ላይ
ማዘዝ እስካልቻለ ድረስ የሥራ ኃይሉን ሸጦ ምንዳውን የሚወስድበት

ለአስተማማኝ ገበያ አገቧን ስላልተፈጠረለት እንደፈለገ ሥራ ማግኘት አይችልም:: ዛሬ በካፒታሊስት አገሮች የሚታየው የሥራ አጦች ያላሰለሰ ዕድገት ሊመነጭ የቻለውም በምርት መገልገያዎች የግል መሆን ምክንያት በማኅበራዊ ምርትና በግላዊ ክፍፍል መካከል በተፈጠረው ቅራኔ መሆኑ ግልጽ ነው:: የምርት መገልገያዎችን የሕዝብ በማድረግ ከብዝበዛ ነፃ የሆነ አዲስ የምርት ግንኙነት በተዘረጋበት በሶሻሊስት ሥርዓት የዜጎችን መሠረታዊ ፍላጐት ማሟላት የፓርቲውና የመንግሥት አንዱ ዓይነተኛ ተልዕኮ በመሆኑ የመሥራት መብት እንዲታወቅና ሕጋዊና ቁሳዊ ዋስትና እንዲያገኝ ተደርጓል:: በዚህም መሠረት እያንዳንዱ ሶሻሊስት ዜጋ "እያንዳንዱ እንደ ችሎታው ለእያንዳንዱ እንደሥራው" በተባለው መርኅ መሠረት በሥራ ተሰማርቶ ለኑሮው ገቢ የማግኘት መብት በሕገመንግሥቱ ስለተረጋገጠለት ከሥራ አጥነት ስጋት ተላቆ ለጋራ ብልጽግናና ለሀገር ዕድገት በመታገል ላይ ይገኛል::

ሶቪየት ኅብረት የመጨረሻውን ሥራ አጥ ዜጋዋን ሥራ በማስያዝ የሠራተኛና ሥራ ማገናኛ ቢሮዋን በ1930 ከዘጋች በኋላ ነበር ዜጎች ሁሉ የመሥራትና በሥራቸው መጠንና ዓይነት የመከፈል መብታቸውን መረጋገጡን የሚደነግግ ሕገመንግሥት በ1936 ያወጣችው::[24] ከ40 ዓመት በኋላ ከዳበረው ሶሻሊስት ኅብረተሰብ ጋር እንዲጣጣም ተደርጎ በ1977 የወጣው ሕገመንግሥት ከቀድሞው በመላቅ የዜጎችን የመሥራትና በሥራ መጠንና ዓይነት የመከፈል መብት ብቻ ሳይሆን "እንደዝንባሌያቸው፣ ችሎታቸው፣ ሙያቸውና ትምህርታቸው" የመሥራት መብትን አረጋግጦላቸዋል::[25] በተለይ ለሴት፣ ወጣትና አካለ ጉዳተኛ ሠራተኞች መብት መጠበቅ ዋስትና የሚሰጡ ልዩ ልዩ ሕጎችም ወጥተዋል::[26]

ሌሎች ሶሻሊስት አገሮችም የሠር ቶአደሩን ሕዝብ ቁሳዊና ባህላዊ ፍላጎቶች ለማሟላት አስተማማኝ የሆነውን ሶሻሊስት ኢኮኖሚያቸውን በመገንባት ሥራ አጥነትን በፍጹም አጥፍተዋል::[27] ሕገጋተ መንግሥታቸውም የመሥራትና እንደ ሥራቸው ዓይነትና መጠን የመከፈል መብታቸውን ለዜጎች አረጋግጠዋል::

የሶሻሊስት አገሮች ዜጎች በዚህ መሠረታዊ መብታቸው በመጠቀም የሥራ አጥነትን ትርጉም ለማወቅ መዝገበ ቃላት እሚያሻቸው ደረጃ በደረሱበት በአሁኑ ወቅት የሥራ አጡ ቁጥር የካፒታሊስት አገሮችን በማጥለቅለቅ ላይ ነው::

## ሠንጠረዥ አንድ

## ከ1965 እስከ 1938 በአለው ጊዜ ውስጥ በየዓመቱ በኅብረተ ሰብእት የካፒታሊስት አገሮች ውስጥ ጠቅላላ ገቢ የነበረውን የሥራ ለተ እድገት የሚያሳይ ሰንጠረዥ /በሺህ የሚቆጠር/

| | አገር | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ጃፓን | ምዕራብ ጀርመን | ፈረንሳይ | እንግሊዝ | ጣሊያን | አሜሪካ |
| 1965 | 390 | 138.0 | 142.0 | 360.0 | 609 | 3520 |
| 1970 | 590 | 148.8 | 262.1 | 612.0 | 1111 | 4088 |
| 1973 | 680 | 273.5 | 393.9 | 618.8 | 1305. | 4304 |
| 1974 | 730 | 582.5 | 497.7 | 614.9 | 1113 | 4076 |
| 1975 | 1000 | 1074.2 | 839.7 | 977.6 | 1230 | 7830 |
| 1976 | 1080 | 1060.3 | 993.5 | 1359.8 | 1426 | 7288 |
| 1977 | 1100 | 1030.0 | 1071.7 | 1483.6 | 1545 | 6885 |
| 1978 | 1240 | 992.9 | 1166.9 | 1390.0 | 1571 | 6046 |
| 1979 | 1170 | 1876.1 | 1349.8 | 1390.5 | 1698 | 5963 |
| 1980 | 1130 | 1036.5 | 1485.4 | 1470.6 | 1703 | 7238 |
| 1981 | 1230 | 1388.6 | 1680.3 | 2419.5 | 1717 | 8746 |
| 1982 | 1310 | 1949.6 | 2034.0 | 3070.6 | 2082 | 10183 |
| 1983 | 1620 | 2487.1 | 2130.0 | 3225.2 | 2218 | 12517 |

ምንጭ መስከረም ቁጽ 5 ቁጥር 19

ገጽ 40

ሠንጠረዥ አንዱ በየአመቱ በማደግ ላይ ያለውን የዳበረ ስድስት ካፒታሊስ አገሮችን የሥራ አጥ መጠን ያመለክታል:: ከ1974 እስከ 1983 ባሉት አሥር ዓመቶች ውስጥ የተመዘገበው የስድስቱ አገሮች ሥራ አጦች ቁጥር እንደሚያመለክተው በየዓመቱ እየጨመረ መጥቷል :: ለምሣሌ በ1974 ከግማሽ ሚሊዮን በላይ የነበረው የእንግሊዝ ሥራ አጥ በ1983 ከስስት ሚሊዮን በላይ ደርሷል :: በዚሁ ጊዜ አምስት ሚሊዮን የነበረው የአሜሪካ ሥራ አጥ ቁጥር ከአሥራ ሁለት ሚሊዮን ዘለል በላይ ገፏል ::

በ1976 በአሜሪካ ከተመዘገቡት ሥራ አጦች መካከል 4,000 የሚሆኑት የዶክትሬት ዲግሪ ያላቸው ሳይንቲስቶች ነበሩ::[28] ይህም አድኃሪው የኢምፔሪያሊዝም የምርት ግንኙነት የምርት ኃይሎችን እድገት አፍኖ መያዙንና በዚህም ሳቢያ በመካከላቸው የተፈጠረው ቅራኔ ማኅበራዊ አብዮትን የሚጋብዝ ፍንጭ እየታየ መሆኑን የሚያመለክት ነው::

ከላይ የተጠቀሰውን ሠንጠረዥ እንደገና ብንማትር ከ1965 እስከ 1976 ባሉት አሥር ዓመቶች የሥራ አጦች ቁጥር በጃፓን 155%፣ በምዕራብ ጀርመን 620%፣ በፈረንሣይ 490%፣ በእንግሊዝ 166%፣ በጣሊያን 102% ዕድገት ማሳየቱን መረዳት እንችላለን:: በነዚህ አገሮች በ1965 የነበረውን የሥራ አጥ ቁጥር ከ1983 ጋር ብናነፃፅረው ዕድገቱ በጃፓን 315%፣ በምዕራብ ጀርመን 1,688% በፈረንሣይ 1,400%፣ በእንግሊዝ 796%፣ በጣሊያን 264%፣ በአሜሪካ 256% ነው ::

ይህን ያህል ከፍተኛ ሥራ አጥ ተሸክመው እያሉ ነው፣

- የኔቶ አገሮች ዓመታዊ የወታደር በጀት 600,000 ሚሊዮን ዶላር የቀን 2,000 ሚሊዮን ዶላር የሆነውና፣

- አሜሪካ ደግሞ በ1975 – 88,900 ሚሊዮን፣ በ1976 – 91,000 ሚሊዮን፣ በ1977 – 104,000 ሚሊዮን፣ በ1978 – 113,000 ሚሊዮን፣ በ1981 – 170,700 ሚሊዮን፣ በ1982 – 226,200 ሚሊዮን፣ በ1983 – 245,500 ሚሊዮን ዶላር ዓመታዊ የወታደር በጀት[29] በመመደብ ማኅበራዊ ልማትን ከማስፋፋትና ለዜጎች የሥራ እድል ከመክፈት ይልቅ ለጥቂት የጦር መሣሪያ ባለኢንዱስትሪዎች ጥቅም በመቆም ለሰው ልጅ ከገጸ ምድር መጥፊያ ዘመናዊ መሣሪያ በማምረት ላይ ያሉት::

## 2.2 የማረፍና የመዝናናት መብት

በአንቀጽ 24 ላይ "ማንኛውም ሰው የማረፍና የመዝናናት መብት አለው – እንዲሁም የተወሰነ የሥራ ሰዓትና ደመወዝ የሚከፈልበት የበዓል እረፍት ቀን" የሚለው የተባበሩት መንግሥታት የሰብዓዊ መብቶች ሁለንታዊ መግለጫ ከወጣ እነሆ ዛሬ 40 ዓመት ሊሆነው ነው:: ሶቭዬት ኅብረት ይህን የዜጎች መሠረታዊ መብት አውቃ በሕገመንግሥቷ ያወጀችው ግን ይህ ሀገሮችን የማስገደድ ኃይል የሌለው ዓለም አቀፋዊ መግለጫ ከመውጣቱ ከ10 ዓመት በፊት ቀድማ ነበር :: ሌሎች ሶሻሊስት አገሮችም የዜጎችን የማረፍና የመዝናናት መብት ሕገመንግሥታዊ ዋስትና በመስጠት ተግባራዊ በማድረግ ላይ ይገኛሉ::[30]

ይህ መብት የሥራ ሰዓትን መቀነስ ይጠይቃል :: በዚህም ምክንያት ዛሬ ብዙ ሶሻሊስት አገሮች በሳምንት 5 ቀን ብቻ በመሥራት ቀዳሚና

ዕሁድን የእረፍት ቀኖች አድርገዋል ። በነዚህ አምስት የሥራ ቀኖችም በሶቪየት ኅብረት 41 ሰዓት፣ ዩጎዝላቪያና ቼኮስሎቫኪያ 42 ሰዓት፣ ቡልጋሪያ 42:30፣ ጀርመን ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ 42:45 እንዲሠራባቸው አድርገዋል ።[31] ይህ በሣምንት የሚሠራበትን ጊዜ ጣሪያ የሚያመለክት እንጂ እንደሥራው ከበደት ዓይነት ከዚህም የሚቀንስበት ሁኔታ አለ ።

ደመወዝ የሚከፈልባቸው የሕዝብ በዓላትና የዓመት ፈቃድ እንዲሁም ይህ መብት በተግባር የሚገለጽበት ሁኔታ በሕግ ተወስኗል።

በሶሻሊስት አገሮች ይህን መብት በሕገ መንግሥታቸው በማወጅ ብቻ አላበቁም። መብቱን ተግባራዊ ለማድረግ የመዝናኛ፣ የባህል ተቋሞች፣ የማረፊያ ቤቶች፣ ክበቦች፣ ስታዲየሞች፣ ሰፋ ሰፋ የስፖርት ቦታዎች፣ ፓርኮች፣ ቤተመጸሐፍት ወዘተ...እንዲቋቋሙ አድርገዋል። በእነዚህ የባህልና የመዝናኛ ተቋሞች በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ሠርቶ አደሮች በመጠቀም ላይ ናቸው።

ሶሻሊስት አገሮች ከላይ የተጠቀሱትን የመዝናኛ ተቋሞች በማደራጀት ብቻ አላቆሙም። ዋጋቸውን በመቀነስ ወይም ነፃ በማድረግ ርምጃ ወስደዋል። ለምሳሌ በሶቪየት ኅብረት 20% የሚሆኑት የማረፊያ ቤቶች ነፃ ሲሆኑ፣ ክፍያ የሚደረግባቸው ገን የ70% ቅናሽ አላቸው።[32]

## 2.3 የጤና እንክብካቤ መብት

በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ለሰው ልጅ ደኅንነትና ጤንነት የሚደረገው እንክብካቤ በጣም ከፍተኛ ነው። — የግለሰብ ደኅንነትና የተሟላ ዕድገት የኅብረተሰቡ ደኅንነትና የተሟላ ዕድገት በመሆኑ፣ይህንንም እውን ለማድረግ የሶሻሊስት አገሮች ሕገ መንግሥት ዜጎች በሚታ

መብት ጊዜ ነፃ የሕክምና አገልግሎት የማግኘት መብት እንዳላቸው በማ
ረጋገጥ ደንግገዋል::[33] ይህም መብት ተግባራዊ ለማድረግም ሕመምን፣
እርጅናንና አካለ ጎደሎነትን የሚሸፍን የማኅበራዊ መድን አገልግሎትን
አደራጅተዋል:: ሆስፒታሎችን፣ ጤና ጣቢያዎችንና ክሊኒኮችንም አስፋፍ
ተው ነፃ ሕክምና በመስጠት ላይ ናቸው::

ከሶሻሊስት አገሮች መካከል ሶቭዬት ኅብረትን ብንወስድ ለዚህ
መብት ሕጋዊ ዋስትና በመስጠትና ተግባራዊ የሚሆንበትንም ስልት በማመ
ልከት በ1977 ሕገመንግሥቱ አንቀጽ 42 ላይ የሚከተለውን ደንግጋ
ለች:-

> የሶቭዬት ዜጎች የጤና እንክብካቤ መብት አላቸው:: ይህ
> መብታቸው መንግሥታዊ የጤና መንከባከቢያ ተቋሞች ዋጋ ባይ
> ከፈሉበት በነፃ ለዜጎች በሚያበረክቱት የተሟላ የሕክምና
> አገልግሎት ተረጋግጦላቸዋል:: ለመታከሚያና ለጤና መንከባ
> ከቢያ የሚሠሩትን ሆስፒታሎች በማስፋፋት፣ የፋብሪካዎች አካ
> ባቢዎች ከጤና ጠንቆች ነፃ እንዲሆኑ ርምጃዎች በሰፊው በመ
> ውሰድ፣ ለሥራ ያልደረሱ ሕፃናት ከትምህርት ጋር ግንኙነት
> ያለውን ሥራ ለመሥራት ካልሆነ በቀር ሥራ ላይ እንዳይሠማሩ
> በማድረግ፣ የበሽታ ጠንቆችን በማጥፋትና በመከላከል ዜጎች
> ሁሉ ረጅም የሕይወት ዘመን ለመኖር እንዲችሉ የሚያበቃ
> የጤና ጥበቃ ዘዴ ምርምር በማስፋፋት ለታዳጊው ትውልድ የሚ
> ደረግለት ልዩ የጤና እንክብካቤ መብት ይረጋገጣል::

በዚህም መሠረት ሶቭዬት ኅብረት የጤና ተቋሞችን በማደራጀት፣
የጤና ባለሙያዎችን በብዛትና በጥራት በማሰልጠን እንዲሁም የሕክምና
መሣሪያዎችና መድኃኒቶችን በማምረት ይህን መብት ጠንካራ ቁሳዊ መሠ
ረት እንዲኖረው አድርጋለች:: በዓለምም ከፍተኛውን ቦታ ይዛለች::
የ1982 ስታትስቲክ እንደሚያመለክተው ለእያንዳንዱ መቶ ሺህ ሕዝብ

385 ዶክተሮችና 1,260 የሆስፒታል አልጋዎች እንዲደርሱት ለዶር ጋሎች:: የታወቀትን ስልጣነት ታላላቅ ካፒታሊስት አገሮች ሁኔታ ከሠ ንጠረዥ ሁለት መመልከት ይቻላል::

ሠንጠረዥ ስስት እንደሚያሳየው ከታላቁ የጥቅምት ሶሻሊስት አብ ዮት ፍንዳታ በፊት ከእያንዳንዱ 1,000 ሕዝብ መካከል 29.1 ሰው ይሞትበት በነበረችው በሶቪየት ኅብረት ዛሬ የሕክምና አገልግሎት በመ ስፋቱ ይህ አሃዝ ወደ 10.3 ዝቅ ሊል ችሏል:: ሠንጠረዡ የሚያሳየው ብጠው ሊሳ አንዱ ቁም ነገር አለ:: በ1913 ብዙ ሰው ለሞት ሲዳ ረግበት ከሌሎች ስልጣነት የዳበሩ ካፒታሊስት አገሮች ሁሉ ሶቪየት ኅብ ረት የመጀመሪያውን ቦታ የያዘች አገር ነበረች:: ዛሬ ግን ይህን ሁኔታ በሚያስደንቅ ሁኔታ ለውጣ በ18.8 ስትቀንስ አሜሪካ የቀነሰ ችው በ3.3 ብቻ ነው:: እንዲያውም ከ1940ው ሁኔታ ጋር ሲነጻጸር የአሜሪካ የሞት መጣኔ በመቀነስ ፈንታ ጨምሮ ይታያል:: ይህም ለማኅ በራዊ ልማት የተሰጠውን ዝቅተኛ ትኩረት የሚጠቁም ነው::

እስቶኒያ የተባለችው አነስተኛዋ የሶቪየት ኅብረት ሪፐብሊክ እን ኳን ለእያንዳንዱ 10,00 ሰው ያዘጋጀቻቸው ዶክተሮች ከእንግሊዝ፣ ከፈረንሳይና ከጣሊያን በእጥፍ ይበልጣሉ:: ከአሜሪካም የምትበልጠው እንዷሁ ወደ እጥፍ ይጠጋል::[34]

## ሠንጠረዥ ሁለት[35]

**በ1982 በሶቪየት ኅብረትና በሌሎች 6 ታላላቅ ካፒታሊስት አገሮች ውስጥ ለያንዳንዱ 100,000 ሰው የነበረትን ደክተሮችና የሆስፒ ታል አልጋዎች የሚያሳይ ሠንጠረዥ**

| ተራ ቁ. | አገሮች | ደክተሮች | የሆስፒታል አልጋዎች |
|---|---|---|---|
| 1 | ሶቪየት ኅብረት | 385 | 1,260 |
| 2 | እንግሊዝ | 164 | 856 |
| 3 | ጣሊያን | 198 | 937 |
| 4 | አሜሪካ | 225 | 646 |
| 5 | ምዕራብ ጀርመን | 259 | 1,160 |
| 6 | ፈረንሳይ | 153 | 1,009 |
| 7 | ጃፓን | 162 | 1,060 |

## ሠንጠረዥ ሦስት[36]

**በሶቪየት ኅብረትና በሌሎች 6 ታላላቅ ካፒታሊስት አገሮች ከያንዳንዱ 1,000 ሕዝብ መካከል የሚሞተውን ሰው የሚያመለክት ሠንጠረዥ::**

| ተራ ቁ. | አገሮች | 1913 /አካባቢ/ | 1940 | 1981 /አካባቢ/ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ሶቪየት ኅብረት | 29.1 | 18.0 | 10.3 |
| 2 | እንግሊዝ | 14.2 | 14.4 | 11.8 |
| 3 | ጣሊያን | 19.3 | 13.6 | 9.7 |
| 4 | አሜሪካ | 13.3 | 10.8[9] | 8.9 |
| 5 | ምዕራብ ጀርመን | – | 11.4* | 11.5 |
| 6 | ፈረንሳይ | 19.0 | 18.9 | 10.1 |

*1938

## 2.4 የጡሮ ዋስትና መብት

የኅብረተሰቡ አባላት የሆኑት ግለሰቦች ሲያረጁ፣ ሲታመሙ ወይም አካለ ስንኩላን ሲሆኑ ኅብረተሰቡ /መንግሥት/ በመርዳት ሊንከባከባቸው ይገባል:: በአጭሩ የጡሮ ዋስትና ሊያገኙ ይገባል ማለት ነው:: ይህም መብት በሰብዓዊ ሠነዶች ተደግፎ መንግሥታት በመብትነት አውቀው ተግባራዊ እንዲያደርጉ የቀረበውን ጥሪ የተቀበሉት አገሮች ብዙም አይደሉም::

ይህ መብት በሶሻሊስት አገሮች ሕገጋተ መንግሥት ታውቆ በየአገሮቹ ተግባራዊ በመሆን ላይ ነው::[37] በነዚህ አገሮች ሕገጋተ መንግሥት መሠረት ዜጎች ሲያረጁ፣ ሲታመሙ፣ በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ አካለ ስንኩላን ሲሆኑ ወይም የቤተሰብ ደጋፊዎች ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ የጡሮ ዋስትና መብታቸው ተከብሮ ለኑሮአቸው አስፈላጊ የሆነ ክፍያ ይሰጣቸዋል::

በሶሻሊስት አገሮች ለዜጎች የሚደረገው ክፍያ "ከእያንዳንዱ እንደችሎታው ለእያንዳንዱ እንደሥራው" በሚለው መርህ መሠረት ቢሆንም በልዩ ልዩ ምክንያቶች መሥራት የማይችሉ ዜጎች ከማኅበራዊ ፍጆታ ሂሣብ ላይ እንዲካፈሉ ይደረጋል:: የጡሮ ዋስትና ተጠቃሚዎችን መሠረታዊ ፍላጎት ሊያሟላ በሚችል ሁኔታ ይህ ሂሣብ በየጊዜው እየጨመረ መጥቷል::[38]

## 2.5 የመማር መብት

ማንኛውም ሰው የመማር መብት እንዳለውና ቢያንስ ቢያንስ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ነፃና ግዴታ መሆን እንዳለበት በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ፊት አባል መንግሥታት በመግባባት መግለጫ ቢያወጡም፣

እንደገና በ1966 በተወሰነው የኢኮኖሚ፣ የሶሻልና የባህል መብቶች ዓለምአቀፍ ስምምነት ቃል ቢገቡም መገለጫውንና ስምምነቱን ተግባራዊ ያደረጉ አገሮች ብዙም አይደሉም::

ትምህርት መማር የዜጎች መሠረታዊ ሕገመንግሥታዊ መብት መሆኑን ሶሻሊስት አገሮች በየሕገመንግሥታቸው አረጋግጠዋል:: የ1936ቱ የሶ ብዬት ኅብረት ሕገመንግሥት የ8 ዓመት የግዴታ ትምህርት ለሁሉም ዜጋ መብትና ግዴታ መሆኑን ደንግጎ ነበር:: ሀገሪቱ ለደረሰችበት የዕድ ገት ደረጃ እንዲጣጣም ተደርጎ የወጣው የ1977 ሕገመንግሥት ደግሞ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ድረስ ነፃ የግዴታ ትምህርት ለሁሉም የሚሰጥ መሆ ኑን ገልጿል::

የ1948ቱ የጀርመን ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት ለዜጎች የ8 ዓመት ነፃ የግዴታ ትምህርት እንደሚሰጥ አረጋግጦ ነበር:: ይሁን እንጂ በ1974 የወጣው ሕገመንግሥት አንድ ርምጃ ወደፊት በመሻገር የ10 አመት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት መማር መብትና ግዴታ መሆኑን ደንግጓል::

የኮሪያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክና የሩማኒያ ሕዝባዊ ሪፐብ ሊክ ዜጎችም የ10 ዓመት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የመማር መብትና ግዴታ አለባቸው:: በሌሎች ሶሻሊስት አገሮች የ8 ዓመት የግዴታ ነፃ ትምህርት የዜጎች መብትና ግዴታ ሆኗል::

ሶሻሊስት አገሮች በየሕገመንግሥታቸው ቃኩትና የሰጡትን ይህን መብት ተግባራዊ የሚያደርጉት የሙያ ትምህርት፣ ልዩ የሁለተኛ ደረጃና የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት፣ የተለዐኮ ትምህርትና የማታ ትምህርት በመማርና መንግ ሥቱም በበኩሉ አስፈላጊውን ድርጅት በማሟላት ነው::

## 2.6 ሌሎች የኢኮኖሚ፣ የሲቪልና የባህል መብቶች

ቀደም ሲል የተዘረዘሩት የኢኮኖሚ፣ የሲቪልና የባህል መብቶች ሶሻሊስት አገሮች ሁሉ በሕገ መንግሥታቸው የደነገጉትና ዋናዎቹ ናቸው:: አንዳንድ ሶሻሊስት አገሮች ለደረሱበት የዕድገት ደረጃ የሚመጥኑ አንዳንድ መብቶችን አውቀዋል:: ለምሣሌ መኖሪያ ቤት የማግኘት መብት፣ በባህል ውጤቶች የመርካት መብት፣ የኮሙኒስት ሥርዓትን ለመገንባት በሚደረገው ዕቅድ መሠረት የሳይንስ፣ የቴክኒክና የሥነ ጥበብ ምርምርን የማካሄድ መብት በመጨረሻው የሶቭዬት ኅብረት ሕገመንግሥት የታወቀ ነው::

ምንም እንኳ የዜጎችን መብትና ግዴታ በሚመለከተው ክፍል ውስጥ ባይደነገግም በሌሎች የሕገ መንግሥቱ ክፍሎች የዜጎችን መብቶች የሚመለከቱ ድንጋጌዎች አሉ:: ለምሣሌ የዜጎች የግለሰብ ንብረት (Personal Property) የማፍራት መብት ተረጋግጧል:: የግለሰብ ንብረት የማፍራት መብት ለትርፍ ባይሆን ቁሳዊና ባህላዊ ፍላጎትን ለማርኪያ እንደመኖሪያ ቤት፣ የግቢ አትክልት፣ መኪና፣ የከብትና የዶሮ ርቢ ወዘተ... የመሳሰሉትን የማፍራትና የማውረስ መብት ነው::

## 3. የሲቪልና የፖለቲካ መብቶችና ነፃነቶች

የዜጎች የሲቪልና የፖለቲካ መብቶችና ነፃነቶች እንደኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ባህላዊ መብቶች የታሪክ ምዕራፋቸው የሚጀምረው ከቅርብ ጊዜ አይደለም:: እነዚህም መብቶችና ነፃነቶች በ17ኛውና በ18ኛው ምዕተ ዓመት የቡርዧው አብዮት በአሜሪካ፣ በእንግሊዝና በፈረንሣይ በተካሄደበት ማግሥት ጀምሮ በየአገሮቹ ታውቀዋል:: ሌሎች አገሮችም በየጊዜው

የሕገጋት መንግሥታቸው አካል በማድረግ ተቀብለዋቸዋል። ይህ ማለት ግን ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ሆነዋል ማለት አይደለም።

ከዜጎች መሠረታዊ የሲቪልና የፖለቲካዊ መብቶችና ነፃነቶች ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው። እነሱም፦

1. የንግግርና የጽሑፍ፣
2. ሰላማዊ ስብሰባና ሰልፍ የማድረግ፣
3. የኅሊና፣
4. በማኅበር የመደራጀት፣
5. በመንግሥታዊና ሕዝባዊ ሥራዎች የመሳተፍ
6. ሌሎች የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ናቸው።

## 3.1 የንግግርና የጽሑፍ ነፃነት

በመሠረቱ የመንግሥታት ይህን ነፃነት በሕገጋት መንግሥታቸው በመደንገግ ሕጋዊ ዋስትና ሰጥተውታል። የንግግርና የጽሑፍ ነፃነት መደባዊ ባህርይ ያለው በመሆኑ በየትኛውም ሥርዓትና አገር የገዥውን መደብ ጥቅሞች ለአደጋ እንዲያጋልጥ አይፈቀድም።

ሶሻሊስት አገሮች የሕዝብን ጥቅም ለማስጠበቅ፣ የሶሻሊስት ሥርዓትን ለማጠናከርና ለማስፋፋት ይህ መብት እንደሚጠቀም በመረጎታቸው በሕገጋት መንግሥታቸው እንዲታቀፍ አድርገዋል። ከዚህ በማለፍ ለመብቱ ተግባራዊነት ትኩረት በመስጠት መብቱ የሚገለፅባቸውን ድርጅቶች ማለትም ማተሚያ ቤቶችን፣ የጽሕፈት መሣሪያዎችን፣ የሕዝብ መሰብሰቢያ አዳራሾችንና አደባባዮችን የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎችን ወዘተ... እንዲሟሉ አድርገዋል፣ በማድረግም ላይ ናቸው።

ይህ መብት ሕጋዊና ቋሚ ቅርጽና ማግኘቱ የሶሺሊስት አገሮች ዜጎች በመንግሥትና በሕዝባዊ ድርጅቶች አሠራር አስተያየት በማቅረብና ለችግሮችም መፍትሔ በመስጠት በዚህ ዲሞክራሲያዊ መብታቸው ተጠቅመው ለአገር ግንባታ የበኩላቸውን ጠቃሚ አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ይጋብዛሉ፡

በካፒታሊስት አገሮችም ይህ መብት የታወቀ ቢሆንም የቡርዧውን መሠረታዊ ጥቅሞች በሚጎዳ ሁኔታ መገለገል አይቻልም፡፡ ለምሣሌ የአሜሪካ ሕገመንግሥት የንግግርና የጽሑፍ ነፃነትን በማጣበብ ኮንግረስ/ፓርላመው/ ሕግ ማውጣት እንደማይችል አረጋግጧል፡፡ ይሁን እንጂ የስሚዝ ሕግ እየተባለ የሚታወቀው ከሕገ መንግሥቱ ጋር የሚቃረን ሕግ በ1940 በኮንግረስ በማውጣቱ ምክንያት ብዙ ኮሙኒስቶችንና ዲሞክራሲያዊ ኃይሎችን አስቃይቷል፡፡ የንግግር ነፃነት አርማ በመባል የታወቀችው እንጀላ ዲቪስ ለሰብዓዊ መብቶች መከበር ባደረገችው ቁርጥ ትግል ተከሰሰች፣ ታሰረች፡፡ ሌላ ወንጀልና ምክንያት ተፈልጎ ከእስር እንዳትወጣ ቢደረግም በሚሊዮን በሚቆጠር የሕዝብ እንቅስቃሴ ግፊት በነፃ ተለቀቀች፡፡ ይሁን እንጂ ሕገመንግሥቱን በመጻረር ኮሙኒስት ናት ተብላ ከነበረችበት ዩኒቨርሲቲ ተባረረች፡፡[39]

## 3.2 ሰላማዊ ስብሰባና ሰልፍ የማድረግ ነፃነት

ሰላማዊ ስብሰባና ሰልፍ የማድረግ ነፃነት የሚገለጸው በመሥሪያ ቤት፣ በመኖሪያ አካባቢ፣ በትምህርት ቤት ወይም በሌላ በማናቸውም አገልግሎት በሚሰጥበት ቦታ በመገኘት በጋራ ጉዳይ ላይ ስብሰባና ውይይት በማድረግና እንዲሁም በአደባባይ፣ በአውራ ጎዳና ወይም በሌላ በማናቸውም ቦታ በመዘዋወር ወይም በመሰብሰብ አስተያየትን በመግለጽ ወይም ውሣኔ በማስተላለፍ ነው፡፡

ይህ ነፃነት በሶሺሊስት አገሮችም ሆነ በካፒታሊስት አገሮች ሕገጋት

የኅሊና ነፃነት በብዙ አገሮች ሕገጋተ መንግሥት ታውቋል:: ይሁን እንጂ አንዳንድ መንግሥታት ከአንድ የሃይማኖት ድርጅት ጋር ራሳቸውን በማቆራኘት በሌሎች ሃይማኖቶች ወይም በአሳማኞች ላይ ተጽዕኖ ሲያሳድሩ ይታያሉ:: ለዚህ መብት ተግባራዊ መሆን መንግሥትና ሃይማኖት* መለያየት ይኖርባቸዋል:: በተመሳሳይ ሁኔታ ትምህርት ቤት ከሃይማኖት ጋር መያያዝ የለበትም::

በሶሻሊስት አገሮች የኅሊና ነፃነት በሃይማኖት የማመንና የማምለክን ወይም ያለማመንና ያለማምለክን መብት ያጠቃልላል:: የኅሊና ዕድገት ከኅብረተሰብ የዕድገት ደረጃ ጋር የተያያዘ እንደመሆኑ በአጠቃላይ መልኩ ሲታይ የሶሻሊስት አገሮች ዜጎች የኅሊና ዕድገት እየዳበረ ነው:: በዚህም ምክንያት አብዛኛው የሶሻሊስት ዜጎች አመለካከት በቁስአካላዊ ርዕዮተዓለም ላይ የተመሠረተ ነው:: ይህ አመለካከት በሃካባዊነት ላይ ከተመሠረተው ከእምነትና ከአምልኮ ተፅዕኖ የተላቀቀ በመሆኑ በዚህ የአስተሳሰብ ክልል ውስጥ የሚገኙ የኅብረተሰብ ክፍሎች የኅሊና ነፃነት ተረጋግጧል:: ይህም ነፃነት ኢ-ሃይማኖታዊ ፕሮፓጋንዳና ቅስቀሳ እስከማሰራጨት ድረስ የሰፋ ነው:: ስለሆነም ወጣቱ ትውልድ ከሃይማኖት ተጽዕኖ ተላቆ የአካባቢውን ነባራዊ ሁኔታ በትክክል ለመረዳት እንዲችል በየትምህርት ቤቶች የማርክሲዝም ሌኒኒዝም ትምህርት በስፋት ይሰጣል::

---

*በዚህ አንቀጹ “ሃይማኖት” የሚለው ቃል አንድ የተወሰነ እምነት ለመመልከት ምዕመናን የሚሰባሰቡበት ድርጅት ድምር ነው:: ይህም በተናጠል የተለያዩ ሃይማኖታዊ ድርጅቶችን የሚያመለክት ሳይሆን ሁሉም በጋራ የሚገለጹበት የወል ስያሜ ነው:: በመሆኑም የእንግሊዘኛውን /Church/ የሚለውን ቃል ለመተርጎም የተጠቀምንበት መሆኑን በአጋጣሚው እናስገነዝባለን::

የዜጎች ንቃተኅሊና ዕድገት በሃባበአዊ ፍልስፍና እንዳይበረዝም ተገ
ቢውን ጥንቃቄ ያደርጋል:: ከሚደረጉትም ጥንቃቄዎች መካከል አንዱና
ዋናው ትምህርት ቤቶችን ከሃይማኖት በመለየት ማንኛውም ሃይማኖታዊ
ድርጅት የራሱን ርዕዮተዓለም በማንፀባረቅ በትምህርት ሂደት ላይ
ምንም ዓይነት ተጽዕኖ እንዳይኖረው ማድረግ ነው::

በሶሻሊስት አገሮች መንግሥት ከሃይማኖት፣ ሃይማኖትም ከመንግሥት
ግንኙነት በሌለው የተለያዩ ድርጅቶች ናቸው:: በመሠረቱ በሶሻሊስት
ሥርዓት የዜጎች እኩልነት በሁለንተናዊ መልኩ የተረጋገጠ ስለሆነ ማን
ኛውም ዜጋ የፈለገውን እምነትና አምልኮ የማመንና የማምለክ መብቱ
ተረጋግጧል:: ይሁን እንጂ ማንኛውም ሰው በፈለገው እምነትና አምልኮ
የሚገለገለው ራሱን ለሶሻሊስት ሕጋዊነት ተገዥ በማድረግ ነው::

መንግሥት ከሃይማኖት የተለየ በመሆኑ ሃይማኖት በመንግሥት ጉዳይ
ውስጥ ማለትም በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚ፣ በማኅበራዊና በሌሎች የመንግሥት
ተግባሮች ውስጥ ጣልቃ አይገባም:: መንግሥትም በሃይማኖት ድርጅቶች መካ
ከል ልዩነት አያደርግም:: መንግሥት የኅብረተሰቡን ጥቅም፣ ሰላምና ደኅ
ንነት የመጠበቅ ሃላፊነት ስላለበት በሃይማኖት ድርጅቶች መካከልና በእም
ነት ምክንያት የሚፈጠሩ ግጭቶችን፣ በሃይማኖት ባቢያ የሚነሱ ለሀገር
አንድነትና ለኅብረተሰቡ ዕድገት እንቅፋት የሚሆኑ ድርጊቶችን ይከሳ
ከሳል::

## 3.4 በማኅበር የመደራጀት ነፃነት

በማኅበር የመደራጀት ነፃነትን ተግባራዊ ማድረግ የሚፈሩት በዝበ
ዟንና ጭቆናን የሚያራምዱ መደቦች ናቸው:: ይህም ያለምክንያት አይደ
ለም:: መደራጀት ኃይል መሆኑንና በተደራጀ ኃይል የሚቀርብ ጥያቄና
የሚወሰዱ ርምጃ እንደሚያንቀጠቅጥ ገዥ መደቦች ያውቃሉ:: ወዘደረም

ለድል የበቃው በዚህ መብት በመጠቀም ባደረገው የተቀናጀ መራራ ትግል መሆኑ ግልጽ ነው::

ከዚህም በቀር ለጸረ አብዮተኞች መጓከም፣ ለሶሻሊዝም ግንባታ መጉለበት የቢሮክራሲያዊ ኃይሎች በየፈርጁ መደራጀት አጋዥ ኃይልን ማጠናከር ነው:: ለዚህም ነው ሶሻሊስት አገሮች አጥብቀው የሚደገፉትና የኅብረተሰቡን በየፈርጁ መደራጀት በመደገፍ ማደራጀት ከተግባሮቻቸው መካከል አንዱ ያደረጉት::

ይህም በመሆኑ የሶሻሊስት አገሮች ሕገጋተ መንግሥት የዜጎችን የመደራጀት መብት አረጋግጠዋል:: ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ በሶሻሊስት አገሮች አያሌ ሕዝባዊ ድርጅቶች፣ የኅብረት ሥራ ማኅበራትና የሙያ ማኅበራት ከመሠረታዊ እስከ አገር አቀፍ ድረስ ተቋቁመው ይገኛሉ::

## 3.5 <u>በመንግሥታዊና ሕዝባዊ ሥራዎች የመሳተፍ መብት</u>

በሶሻሊስት አገሮች የሕዝብ ሉአላዊ ሥልጣን ከሚገለጥባቸው መስኮች ዋናው ዜጎች ልዩ ልዩ የመንግሥታዊና ሕዝባዊ ድርጅቶችን ሥራዎች በመምራትና በመቆጣጠር ያላቸው ከፍተኛና ንቁ ተሳትፎ ነው::

ይህም ለሥልጣን አካላት/የሕዝብ ሸንጎዎች/ በመምረጥና በመመረጥ፣ የሸንጎ አባላት እንዲሆኑ ለመረጧቸው ወኪሎቻቸው መመሪያዎች በመስጠት፣ የወኪሎቻቸውን ሪፖርት በማዳመጥ፣ በውሣኔ ሕዝብ በመሳተፍ አስፈላጊውን በማድረግ፣ በመሠረታዊ ሕጎች ረቂቅ ላይ አስተያየት በመስጠትና በሕዝባዊ ሸንጎዎች ሥራ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በመሳተፍ ይገለጧል:: በዚህም ሕዝቡ የመንግሥቱንና የሕዝባዊ ድርጅቶችን አሠራር መቆጣጠር ይችላል:: የሕዝቡን ገንቢ አስተያየት በመቀበል መንግሥታዊና ሕዝባዊ ድርጅቶች ስህተቶችን እንዲያርሙ ይረዳቸዋል:: እንዲያውም

ሕገጋተ መንግሥቱ መንግሥታዊና ሕዝባዊ ድርጅቶች በአሠራራቸው የፈጸሟ ቸውን ሊታረሙ የሚገባቸው ስህተቶች እንዲያርሙ ከዜጎች የቀረበውን አስተያየት ተቀብለው መልስ የመስጠት ግዴታ እንዳለባቸው ያመለክታሉ። በሆነ አቀራረቦች ላይም ክትትል እንዳያደርጉ በመከልከል ይህ ዓይነቱ ተግባር የሚያስቀጣ መሆኑን በመደንገግ ሕጋዊ ዋስትና ሰጥተዋል።

የሶሻሊስት መንግሥት አደረጃጀትና አሠራር ሕዝብን በሰፊው የሚያ ሳትፍ በመሆኑ በሕዝብና በመንግሥት መካከል ያለው የሰመረ ግንኙነት በዓላማ አንድነት ላይ የተመሠረተ ነው። በመሆኑም በመካከላቸው ቅራኔ የለም። የሕዝብ፣ ለሕዝብ፣ ባለሕዝብ የሆነ መንግሥት በመሆኑ ይህ ከሌሎች የመደብ ዲሞክራሲዎች ሁሉ የቦሻሊገተ ዲሞክራሲን የበላይነትና መዳበር የሚያመለክት ነው። በዚህ መብት በመገልገል በአንድ ወቅት በተለያዩ ደረጃዎች ለተቋቋሙት ሸንጎዎች ብቻ በሶቭየት ኅብረት በ2.2 ሚሊዮን በላይ፣ በጀርመን ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ከ203,000 በላይ የሕዝብ እንደራሴዎች ተመርጠው በመሥራት ላይ ነበሩ።[42]

## 3.6 ሌሎች የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች

ከዚህ በላይ ከተዘረዘሩት በተጨማሪ በሶሻሊስት አገሮች ሕገመንግ ስታዊ ዋስትና ያገኙ ሌሎች መብቶች አሉ።

ማንኛውም ዜጋ/ሰው/ በባለሥልጣኖች ወይም በሌሎች ግለሰቦች እን ዳይደፈር በመንግሥትና በሌሎች ሕጎች ሰውነቱ ተጠብቋል። ይህም ሕጋ ባልሆነ መንገድ ያለመያዝና ያለመፈተሽ መብትን የሚጨምር ነው። ግለ ሰቡ ወንጀል ለመፈፀሙ ከተጠረጠረ ገን ሕግ በሚያዘው ሁኔታ በሕግ ሥል ጣን የተሰጠው ወገን ተጠርጣሪውን ሊይዘው ወይም ሊፈትሸው ይችላል።

የመኖሪያ ቤት ያለመደፈር መብት ሌላው ሕገመንግሥታዊ መብት ነው።

የመኖሪያ ቤት መደፈር የሚሆነው ማንም ሰው ተከራይቶ ወይም ሠርቶ ከሚኖርበት ቤቱ ወይም ቅጥር ግቢ ውስጥ ግልጽ የሆነ ተቃውሞ እያሰማ የሌላ ሰው መግባት፣ የገባ ሰው ከቤት እንዲወጣ በግልጽ ሲጠየቅ እምቢ ብሎ መኖር፣ ወይም በዘመናዊ የቴክኒክ መሳሪያዎች በመጠቀም በመኖሪያ ቤት ውስጥ የሚከናወነውን ነገር መከታተል ነው።[43] ይሁን እንጂ እንደውሃ፣ ኤሌትሪክና የመሳሰሉትን አገልግሎቶች ለመስጠት ወይም የአገልግሎት ዋጋ ለመቀበል ወይም ወደሌላው ኅብረተሰብ ሊተላለፍ የሚችል ማናቸውንም ዓይነት አደጋ ለማስወገድ አገባብ ያላቸው ባለሥልጣኖች /ገለሰቦች/ ሊገቡ ይችላሉ። ከዚህም በቀር ወንጀል በመፈጸሙ ወይም በወንጀል በመጠርጠሩ መያዝ፣ ቢቶም መበርበር ያለበት ከሆነ ከሚመለከተው የመንግሥት አካል /ፍርድ ቤት ወይም ዐቃቤ ሕግ/ የመያዣ ወይም የመበርበሪያ ፍቃዱ በመያዝ ሕግ በሚወስነው መሠረት ከነዋሪው ፍላጎት ውጭ ቢሆንም መኖሪያ ቤት ወይም ቅጥር ግቢው ውስጥ መግባት ይቻላል።

የግለ ደብዳቤዎች፣ የስልክ ውይይቶችና የቴሌግራፍ ግንኙነቶች ባለቤቶቹ የሚመለከታቸው ባለአድራሻዎች ብቻ በመሆናቸው ማንም ሌላ ሰው ወይም ባለሥልጣን ጣልቃ ገብቶ ማወቅ አይችልም። በመሆኑም ይህ የመልዕክት ልውውጥ አለመደፈር መብት የተጠበቀ ነው።

ቤተሰብ የመንግሥትን ጥበቃ የሚያገኝ መሆኑ፣ እንዲሁም በመንግሥትና ሕዝባዊ ድርጅቶች ድርጊቶች ላይ ተቃውሞ የማቅረብ መብት ዜጎች ያላቸው መሆኑ በሕገ መንግሥት የተደነገጉ ዋስትናዎች ናቸው።

## 4. የዜጎች መሠረታዊ ግዴታዎች

ከዚህ በላይ ስለዜጎች መሠረታዊ ሕገመንግሥታዊ መብቶች ለመግለጽ ተሞክሯል። በመብቶችና በግዴታዎች መካከል ስላለው ዲያሌክቲካዊ ግን

ኙነትም በአጭሩ ለማስገንዘብ ጥረት ተደርጓል:: ከዚህ በመቀጠል ደግሞ የዜጎችን መሠረታዊ ሕገመንግሥታዊ ግዴታዎች ባጭሩ እንመለከታለን::

ዜጎች ለሚገኙበት ሶሻሊስት ኅብረተሰብና ለመንግሥታቸው በማድረግ ማከናወን የሚገባቸው ዋና ዋናዎቹ ሕገመንግሥታዊ ግዴታዎች ሕግን ማክበር፣ የሥራ ሥነሥርዓትን ማክበር፣ ሶሻሊስት ንብረትን መንከባከብና መጠበቅ፣ የመንግሥትን ጥቅሞች መጠበቅና አገርን ከጠላት መከላከል እንዲሁም ግብር መክፈል ናቸው::

በሶሻሊስት አገሮች ሕገጋተ መንግሥት መሠረት ዜጎች ሕገመንግሥቱን፣ ሌሎች ሕጎችንና ሶሻሊስት ሥነምግባርን የማክበር ግዴታ አለባቸው:: የዜጎች መብቶች ሕጋዊ ዋስትና የተሰጣቸው በሕገመንግሥትና በሌሎች ሕጎች በመሆኑ፣እንዲሁም በምርት መገልገያዎች ማኅበራዊ መሆን ብዝበዛና ጭቆና ተወግዶ የተመሰረተውን አዲስ ኅብረተሰብ ለማጠናከር የተወሰደውን ርምጃ ሕጋዊ በማድረግ የሠርቶ አደሩን ሕዝብ ጥቅሞች የሚጠብቁ፣ ፍላጎቱን የሚያሟሉት እነዚህ ሕጎች በመሆናቸው ያለአንዳች ማወላወል በዜጎች መከበር አለባቸው:: ሶሻሊስት ሕጋዊነት የሚሰፍነውም ዜጎች ይህን ግዴታቸውን ሲወጡ ነው::

ሌላው ሕገመንግሥታዊ ግዴታ በሶሻሊስት ሥራ ሥነሥርዓትን ማክበር ነው:: በመሠረቱ ሥራ መሥራት የዜጋ መብት ቢሆንም፣ አካለ ሙሉ የሆነ ማንኛውም ዜጋ በተመደበበት የሥራ መስክ ሁሉ የሥራ ሥነሥርዓትን አክብሮ በቅን ልቡና ተግባሩን ማከናወን ግዴታው ጭምር ነው::

የሶሻሊስት አገሮች ዜጎች ሶሻሊስት ንብረትን የመጠበቅና የመንከባከብ ግዴታ አለባቸው:: የመንግሥትንና የሕዝብን ንብረት ከምዝበራና ከብኩንነት የመከላከል ግዴታ በዜጎች ላይ ተጥሏል::

ዜጎች የመንግሥትን ጥቅም፣ ሥልጣንና ክብሩን መጠበቅ፣ ሶሻሊስት
እናት አገርን ከጠላት መከላከል፣ እንዲሁም በጦር ኃይሉ ውስጥ ተደ
ልደሉ የውትድርና አገልግሎት ማበርከት የክብር ግዴታቸው ነው::

ዜጎች ለመንግሥታቸው ግብር የመክፈል ግዴታ እንዳለባቸው በአንዳ
ንዱ አገሮች ሕገ መንግሥት ተደንግጓል:: የአልባኒያ ሕዝባዊ ሪፑ
ብሊክና የቡልጋሪያ ሕዝባዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት በቅደም ተከተል
በአንቀጽ 33/1/ እና በአንቀጽ 94 ይህንኑ አረጋግጠዋል::

ከዚህ በላይ የተመለከቱት መሠረታዊ የዜጎች ግዴታዎች በብዙ ሶሻ
ሊስት አገሮች ሕገ መንግሥት የተገለጹት ናቸው:: በሁሉም ሶሻሊ
ስት አገሮች ሕገ መንግሥት ውስጥ ያልተደነገጉ፣ ነገር ግን በአ
ንዳንድ አገሮች ሕገ መንግሥት ውስጥ የተመለከቱ ሌሎች የዜጎች
ግዴታዎች አሉ:: ከዚህም መካከል የሌሎችን መብት የማክበር ግዴታ፣
በብሔሮችና በብሔረሰቦች መካከል ያለውን ግንኙነት የማጠናከር ግዴታ፣
የራስን ልጅ አንከባክቦ የማሳደግ ግዴታ፣ ከሌሎች አገሮች ሕዝቦች ጋር
ወዳጅነትና ትብብርን የማጠናከር ዓለም አቀፋዊ ግዴታ፣ ታሪካዊ ቦታዎ
ችንና የባህል ቅርሶችን ተንከባክቦ የመጠበቅ ግዴታ ይገኙበታል::[44]

የሌሎች አገሮች ዜጎች የሆኑ ወይም ዜግአልባ የውጭ አገር ሰዎች
አንዳንድ መሠረታዊ ግዴታዎች አሉባቸው:: ለምሳሌ በሶቭዬት ኅብረት
የሚኖሩ እነዚህ ሰዎች ሕግ የማክበር፣ ግብር የመክፈል፣ ሥራ ከመ
ሥራት መብታቸው አኳያ የሥራ ሥነሥርዓትን የማክበር ግዴታ አለባቸው::[45]

## መደምደሚያ

"ከጥንት የጋርዮሽ ኅብረተሰብ በስተቀር "እስከዛሬ ድረስ ያለው የኅብረተሰብ ታሪክ ሁሉ የመደብ ትግል ታሪክ ነው" በማለት ነበር የወዛደሩ መሪዎች ማርክስና ኢንግልስ የዛሬ 140 ዓመት ገደማ የኮሙኒስት ፓርቲ ማኒፌስቶን የመጀመሪያ ዐረፍተ ነገር መጻፍ የጀመሩት፡፡ ይህ የመደብ ትግል ያስመዘገበው ታሪክም በአንድ በኩል ከብዝበዛና ከጭቆና ነፃ የመውጣት መብትን፣ በሌላ በኩል ደግሞ የመበዝበዝና የመጨቆን መብትን ለማረጋገጥ የተደረገውንና በመደረግ ላይ ያለውን የተፃራሪ መደቦች ፍልሚያ ነው፡፡ በዚህ የመደብ ትግል ሂደት የመሸነፍና የማሸነፍ፣ በከፊልም ሆነ በሙሉ የማጣትና የማግኘት በየቀሉ የመደቦች ሹም ሽር ተከስቷል፡፡

በአጠቃላይ መልኩ ሲታይ ከመራራ ትግል በኋላ በተገኘው የመደቦች ሹም ሽር ባቢያ የሠርቶ አደሩ ሕዝብ መብትና ነፃነት ዕድገት እያሳየ መጥቷል፡፡ በዚህም መሠረት ሰፊው ሕዝብ ከባሪያ አሳዳሪው ሥርዓት ይልቅ በፊውዳሉ ሥርዓት የተሻለ መብትና ነፃነት አይቷል፡፡ የካፒታሊስቱ ሥርዓት ደግሞ ከሁለቱ ቀደምት ሥርዓቶች የተሻለ መሆኑን በተግባር አስመስክሯል፡፡ ቀደም ሲል በዝርዝር እንደተመለከትነው የሶሻሊስት ኅብረተሰብ በዓይነቱ አዲስና ሰፊ የሆነ መብትና ነፃነት ለአባላቱ ሁሉ በማቀዳጀት ከሁሉም በመላቁ ረገድ ሪኮርዱን ይዟል፡፡

በራሱ በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ውስጥም ቢሆን የዜጎች መብትና ገጽታ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየዳበረ መጥቷል፡፡ ለምሳሌ የመጀመሪያዋ ሶሻሊስት አገር ሁኔታ ብንመለከት ሶቭዬት ኅብረት በ1918 ባወጣቸው ሕገመንግሥት የዜጎች መሠረታዊ የሶሻል፣ የኢኮኖሚና የባህል መብቶች አልታወቁም ነበር፡፡ እንዲያውም በወቅቱ ተጨባጭ ሁኔታ አስገዳጅነት የወደቀው አዱ

ሃሪ ሥርዓት ተቆርቋሪዎች የፖለቲካ መብቶችን ተነፍገው ነበር:: ከቆጠመው ዕድገት በማሳየት የ1936 ሕገመንግሥት የፖለቲካ፣ የሶሻል፣ የኢኮኖሚና የባህል መብቶችንና ነፃነቶችን ለሰጠዶት ኅብረት ዜጎች ሁሉ ሰጥቷል::

ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ የተፈጠሩት የሌሎች ሶሻሊስት አገሮች ሕገጋተ መንግሥትም እንደሚያረጋግጡት የየሀገሮቹ ዜጎች በነዚህ መብቶችና ነፃነቶች ተጠቃሚዎች ሆነዋል:: የዳበረው ሶሻሊስት ኅብረተ ሰብ ነፀብራቅ የሆነው የ1977 የሶቪየት ኅብረት ሕገመንግሥት የዜጎች መሠረታዊ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊና የባህል መብቶችና ነፃነቶች ከፍተኛ የዕድገት ደረጃ ላይ መድረሳቸውን የሚያመለክት ታሳቢ ሰነድ በመሆኑ ሌሎች ሶሻሊስትና የሶሻሊስት ዕድገት ፈለግ ተከታይ አገሮች በየፊናቸው ለመጠበቅ የሚታገሉለት አንደኛው የግብ ሰነድ ነው::

የፊውዶ ቡርዧውን ሥርዓት ያስተናገደቸውን ኢትዮጵያን ብንመለከት በ1923 ከወጣው ሕገመንግሥት ይልቅ በ1948 የወጣው ሕገመንግሥት በሁሉም ገጽታው የተሻለ ሆና ይታያል:: መሻሉ የገዥውን መደብ ጥቅሞች ከመስከበር አንጻር ሲመዘን እንጂ ሁለቱም ቢሆኑ ለጭቁኑ ሠርቶ አደር ሕዝብ ፋይዳ አልነበራቸውም:: በመሆኑም ነው መስከረም 2 ቀን 1967 የጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥትን ያቋቋመው አዋጁ ይህን ሕገመንግሥት በማገዱ "ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የማኅበራዊ ኑሮ፣ የፖለቲካ አስተሳሰብና ለአገሪቱ የኢኮኖሚ ዕድገት በሚበጅና <u>ሰብዓዊ መብቶችን</u> በሚያስከብር መልክ ተዘጋጅቶ" ሌላ ሕገመንግሥት ይወጣል[46] በማለት የደነገገው::

ይወጣል የተባለው ሕገመንግሥት መወለዱ ከሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ጋር ከመያያዙም በላይ አዲስ ሕዝባዊ የፖለቲካ፣

የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ሥርዓት የሚመሠረተ፣ የመንግሥትን መዋቅር፣ የሥልጣንና የአስተዳደር አካላትን አመሠራረትና አሠራር የሚወስን፣ መሠረታዊ የዜጎች መብቶችና ነፃነቶችን የሚያረጋግጥ፣ እንዲሁም ሌሎችን መሠረታዊ ጉዳዮች የሚሸፍን በመሆኑ ጥናቱና ዝግጅቱ ረዥም ጊዜ ሊወስዱ ቻሏል::

ጓዱ አብዮታዊው መሪያችን ለኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ ስድስተኛ መደበኛ ስብሰባ ባቀረቡት ማዕከላዊ ሪፖርት እንደገለጹት "የሕገመንግሥቱን ረቂቅ አጠናክሮ ከማዘጋጀት ጀምሮ በሕዝብ አስተያየት ተሰጥቶበት እንዲዳብር፣ ከዚያም በጥራት እንዲቀነባበር ለማድረግ አንዱ የሕዝቡን ፍላጎት ሊያሟላ የሚችል ብቁ የሕገመንግሥት ኮሚሽን" ይቋቋማል:: የኮሚሽኑ ተልዕኮም ሆነ የሪፑብሊክን ምሥረታ ለማደናቀፍ የሚያደርጉ ጠላቶች እንዳሉብን በማስገንዘብ ጓዱ ዋና ፀሐፊው "...ይህንን የሕዝባዊ ሥልጣን ማረጋገጫና የሶሻሊዝም ግንባታ ዋስትና የሆነ እርምጃ ለማኮሸፍ የማይሰነዝሩት የጥቃት ዓይነት አይኖርም"እንዳሉት በተለይ በሌሎች ሶሻሊስት አገሮች ላይ እንደተጠቀመው ሁሉ ኢምፔሪያሊዝም በሕዝብ ሉአላዊ ሥልጣን፣ መብቶችና ነፃነቶች ላይ የሚያደርገው የተለመደ ነቆራና የማጥላላት ፕሮፓጋንዳ አንዱ የተገለ መሣሪያው በመሆኑ ተዘጋጅቶ መጠበቅ ገዱ ይሆናል::

በዚች አገር አብዮት ከፈነዳበት ጊዜ ጀምሮ በየመስኩ አያሌ አኩሪ ድሎች ተመዝግበዋል:: ዋና ዋናዎቹ የምርት መገልገያዎች በመንግሥትና በሕዝብ ይዞታ ሥር ውለዋል:: ብዝበዛን ጨርሶ ለማስወገድ ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ላይ ነው:: በትምህርት፣ በጤና፣ በኑሮ ዋስትና፣ በመዝናኛ አገልግሎት፣ በባህል ዕድገትና መሳሳት የሚደነቁ ውጤቶች ተገኝተዋል:: የምርት ሀይሎችን በማሳደግ ለሶሻሊዝም ተፈላጊውን ቁሳዊ

ቴክኒካዊ መሠረት ለመጣል በየክፍለ ኢኮኖሚው አመርቂ ተግባሮች ተከናው
ነዋል:: ለበለጠ ውጤት መገኘትና ለዘላቂው ግብ መዳረሻ አስፈላጊው
ሁሉ እየተደረገ ነው:: ሠርቶ አደሩ ሕዝብ የመንግሥት ሥልጣን ባለቤት
በሚያደርገው ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት ንቁ ተካተፍ ለማድረግ የሚ
ያስችለውን ልምድ ቀደም ሲል ከተቋቋሙት ሕዝባዊ ድርጅቶች ቀስሟል::
በየአጋጣሚው የሶሻሊስት አገሮች የበለጸገ ልምድ በሕዝብ መገናኛ ዘዴ
ዎች ለማካኝነት እየቀረበ በቂ ገንዘብ ተወስዷል:: የነዚህ ቀደም ሁኔ
ታዎች መመቻቸት የዜጎችን መሠረታዊ መብቶች፣ ነፃነቶችና ግዴታዎች በሕ
ዝባዊት ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ እውን ለማድረግ የሚያስችሉ
አስፈላጊና ጠቃሚ መሠረቶች ናቸው::

የዜጎች መሠረታዊ መብቶችና ግዴታዎች መታወቅና መከበር በመንግሥ
ትና በዜጎች መካከል በዓላማ አንድነት ላይ የተመሠረተ የሰመረ ግንኙ
ነት እንዲኖር ያደርጋል:: መብቶችንና ግዴታዎችን ተግባራዊ ለማድረግ
የሚቻለው መንግሥታዊና ሕዝባዊ ድርጅቶች፣ ባለሥልጣኖችና ግለሰቦች
ሕገመንግሥትን፣ ሌሎች ሕጎችንና የመንግሥት መመሪያዎችን ያለአንዳች
ማወላወል በትክክል በማክበርና በማስከበር ሶሻሊስት ሕጋዊነት እንዲሰ
ፍን በማድረግ ነው:: በመሆኑም ሶሻሊስቱ ሕጋዊነትን ለማስፈን የተለየ
ተልዕኮ የተሰጣቸው ድርጅቶች፣ ባለሥልጣኖችና ግለሰቦች ሁሉ የሥራ ድር
ሻቸውን፣ ሥልጣንና ኃላፊነታቸውን በትክክል በመወጣት በሕዝባዊት ዲሞ
ክራሲያዊት ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ ሕገመንግሥት የሚረጋገጡትን የዜጎች መሠ
ረታዊ መብቶችና ግዴታዎች እንዲከበሩ ማድረግ ይኖርባቸዋል::

በት.መ.ማ.ማ.ድርጅት ታተመ ።

proudly brought to you by

www.binyamhk.wordpress.com

